ጥሙት ሰማንያ ስድስት ይሆናል ፤ ሰማንያ ስድስቱ አንድ ኢዮቤልዩ ሆኖ ሠላሳ ሰባት ዘመን ይተርፋል ፤ ሠላሳ ሰባቱ ዘመን አምስት ሱባዔ ሆኖ ሁለት ዘመን ይተርፋል ::

፴፮፤ ወበዐሥር ወሐምስ ኢዮቤልዩ በሱባዔ ሣልስ ነሥአ ሎቱ ላሜህ ብእሲተ ፤
ባሥራ አምስተኛው ኢዮቤልዩ በሦስተኛው ሱባዔ ላሜህ ሚስት ልትሆነው ወሰደ ፤
ወስማ ቤቴኖስ ፤
ስሟም ቤቴኖስ ትባላለች ፤
ወለተ በራኪኤል ወለተ እኅተ አቡሁ ሎቱ ብእሲተ ፤
ሚስት ትሆነው ዘንድ የአባቱን እኅት የበራኪኤልን ልጅ ቤቴኖስን ወሰደ::

ምዕራፍ ፮

፩፤ ወበዝ ሱባዔ ወለደት ሎቱ ወልደ ፤
በዚህ ሱባዔ ወንድ ልጅ ወለደችለት ፤ ላሜህ ኖኅን በሰማንያ ሁለት ዘመን ወልዶታል ፤
ቢያገናኙት ሰባት መቶ ሃምሳ ስድስት ይሆናል ፤ ዐሥራ አራት ሱባዔ ሁኖ ሰባ ዘመን ይተርፋል ፤ ከሰባው አርባ ዘጠኝ ሲነ ሣለት ሃያ አንድ ዘመን ይቀራል ፤ ይህንም በሱባዔ ቢገቡት ሦስት ሱባዔ ይሆናል ፤
ወጸውአ ስሞ ኖኅ ፤
ስሙን ኖኅ አለው ፤ ኖኅ ማለት ዕረፍት ፤ ትፍሥሕት ፤ተረፍ፤ ማለት ነው ፤
እንዘ ይብል ዘይናዝዘኒ እምኵሉ ግብርየ ፤
ከሥራዬ ሁሉ የሚያሳርፈኝ ይህ ነው ሲል ዕረፍት አለ ፤
ወእምኵሉ ኃዘንየ ፤
ከኃዘኔ ሁሉ የሚያረጋጋኝ ሲል ትፍሥሕት አለ ፤
ወእምድርኒ እንተ ረገማ እግዚአብሔር ፤
እግዚአብሔር ከረገማት ከፈረደባት ምድር ይቀራል ሲል ተረፍ አለ ::

፪፤ ወበፍጻሜሁ ለዐሥር ወታ ስዕ ኢዮቤልዩ ፤
ባስራ ዘጠነኛው ኢዮቤልዩ መጨረሻ ፤

በሱባዔ ሳብዕ ወበሳድስ ዓመቱ ሎቱ ሞተ አዳም ፤
በስልሳኛው ሱባዔ በስድስተኛው ዓመት አዳም ሞተ ፤
ወቀበርዎ ኩሎሙ ደቂቁ ውስተ ምድረ ፍጥረቱ ፤
ልጆቹ በተፈጠረባት ቦታ በቀራንዮ ቀበሩት ::

፫፤ ወውእቱ መቅድመ ተቀብረ ውስተ ምድር ፤
ከሁሉ አስቀድሞ እሱ በምድር ተቀበረ አቤልን ሳይቀብሩት ቀርቶአልና እን ዲህ አለ ፤ መቅድመ ለሴት ነው እንጂ ለአቤል አይደለም የአዳም ዘመኑ ዘጠኝ መቶ ሠላሳ ነው ፤
በኢዮቤልዩ ግን አይቆጥሩም ፤
ወሮ ዓመተ አሕፀፀ እም ፲፪ ፤
ከሺው ዘመን ሰባ ዘመን አጎደለ ፤
እስመ ፲፪ ዓመት ከመ አሐቲ ዕለት ውስተ ስምዓ ሰማያት ፤
ሺሑ ዘመን በመላእክት ልቡና አንድም በልበ ሥላሴ እንደ አንዲት ቀን ናትና ::

፬፤ በእንተ ዝንቱ ተጽሕፈ በእንተ ዕፀ አእምሮ ፤
ስለዚህ ነገር የዕፀ በለስ ነገር ተጻፈ ፤
እስመ በዕለተ ትበልዑ እምኔሁ ትመውቱ ፤
ከዚህ ዕፀ በለስ በበላች ሁበት ቀን ትሞታላችሁ ብሏቸዋልና፤
በእንተ ዝንቱ ኢፈጸመ ዓመታተ ዛቲ ዕለት ፤
ስለዚህ ነገር ያንዲቱ ቀን ዘመን አልተፈጸመም ፤
እስመ ባቲ ሞተ ፤
በዚህች ቀን ሞቶባታልና::

፭፤ ወበተፍጻሜቱ ለዝንቱ ኢዮቤልው ፤
በዚህ ኢዮቤልው መጨረሻ፤
ተቀትለ ቃየል እምድኅሬሁ በ፩ ዓመት ፤
አዳም ከሞተ በኋላ በአንድ ዓመት ቃየል ሞተ ፤
ወወድቀ ላዕሌሁ ቤቱ ፤
በላዩ ላይ ቤቱ ተናደ ፤
ወሞተ በማዕከለ ቤቱ ፤
በቤቱ ውስጥ ሞተ ፤
ወተቀትለ በአዕባኒሃ ፤

በድንጋይም ሞተ ፣ አሪት በድንጋይ ሞተ ትላለች ፤ ከዚህ ቤት ተጭኖት ሞተ አለ ፤ ይህ አይጣላም ቢሉ አይጣላም በፊት በድንጋይ መትቶታል ተሸክመው ወስ ደው ከቤቱ አስተኝተውት ሳለ ቤቱ ተንዶ ተጭኖት ሞቷል ፤

እስመ በዕብን ቀተሎ ለአቤል ፤

አቤልን በድንጋይ ገድሎታ ልና ፤

ወበዕብን ተቀትለ በኵነኔ ጽድቅ፤

በእውነተኛ ፍርድ በድንጋይ ሞተ ::

፮፤ ወበእንተዝ ተሠርዐ ውስተ ጽላተ ሰማይ ፤

ስለዚህ ነገር በመላእክት ልቡና ፣ አንድም በሰሌዳ ሰማይ ተጽፏል ፤

በንዋይ ዘቀተለ ብእሲ ቢጸ ቦቱ ይትቀተል ፤

ባልጀራውን የገደለ ሰው በገደለበት ይሙት ተብሎ ተጽፏል ፤

በከመ አቀሰሎ ከማሁ ይግበሩ ቦቱ ፤

እንደ አቄሰለው ያቀሰ ሉት::

፯፤ ወበሳ ወሯቱ ኢዮቤልዩ ነሥአ ሎቱ ኖኅ ብእሲተ ፤

በዛያ አምስተኛው ኢዮቤ ልዩ ኖኅ ሚስትን አገባ ፤

ወስማ አምዛራ ፤

ስሟም አምዛራ ይባላል ፤ አሞዛራ፤ አምዛው ይላል ፤

ወለተራዚኤል ወለተ አኀቱ ሎቱ ብእሲተ ፤

የእህቱ ልጅ የምትሆን የራዚኤልን ልጅ ሚስት ትሆነው ዘንድ ወሰደ ::

፰፤ በቀዳሚ ዓመት ፣ በሱባዔ ሐምስ ወበሣልስ ዓመቱ ፤

በመጀሪያው ዓመት ባምስተ ኛው ሱባዔ በሦስተኛው ዓመት ፤

ወለደት ሎቱ ሴምሃ ፤

ሴምን ወለደችለት ፣ ኖኅ ሴምን ባምስት መቶ ዘመን ወልዶታል ቢያገናኙት ሽሕ ሁለት መቶ አምሳ ስድስት ይሆናል ይህ ሽሕ ሁለት መቶ አምሳ ስድስቱ ኻያ አራት ኢዮቤልዩ ሁኖ ኻያ አራት ዘመን ይተርፋል ፤

ይህን ኻያ አራቱን ዘመን ከአምሳ ስድስቱ ሲጨ ምሩት ሰማንያ ይሆናል ፤ ከሰማንያው አርባ ዘጠኙ አንድ ኢዮቤልዩ ሆኖ ሠላሳ አንድ ዘመን ይተርፋል ፤ ሠላሳው አራት ሱባዔ ሁኖ ሦስት ዘመን ይተርፋል ፤ ኢዮቤልዩ የሚለው ኩመ ቶው ሁለቱን ዘመን አን ስቶ አርባ ዘጠኙን ዘመን ነው ፤ ይህን ያህል ዘመን ይተርፋል አያልን ያመጣ ነው ከመቶው ሁለት ፤ ከመቶው ሁለት ዘመን ያነሣነው ነው፤ሺሑ ሁለት መቶ አሥራ ሁለት ዓመት ነው ፤ ዘጠኝ ሲነሱለት ሠላሳ አንድ ይቀራል ፤ ይህን በሱባዔ ሲገቡት ሦስት ሱባዔ ሁኖ ሶስት ዘመን ይተርፋል ፤ ሱባዔ ሐምስ ማለቱ ስለተጀመረ ነው ፤

ወበሐምስ ዓመቱ ወለደት ሎቱ ካምሃ ፤

ባምስተኛው ሱባዔ ካምን ወለደችለት ፤

ወበዓመት ቀዳሚት በሱባዔ ሳድስ ወለደት ሎቱ ያፌትሃ ፤

በመጀመሪያው ዓመት በስ ድስተኛው ሱባዔ ያፌትን ወለደችለት ::

፱፤ ወኮነ አመ ወጠኑ ደቂቀ ዕጓለ እመሕያው ይብዝኑ ዲበ ገጸ ኩላ ምድር ፤

የአዳም ልጆች በዚህ ዓለም ይበዙ ዘንድ በጀመሩ ጊዜ እንዲህ ሆነ ፤

ወአዋልድ ተወልዳ ሎሙ ፤

ኮነ ያለውን ተወልዳ ብሎ ተረጐመው ሴቶች ልጆች ተወለዱላቸው ፤

ወርእይዎን መላእክተ እግዚአብ ሔር በአሐቲ ዓመት ዘኢዮቤልዩ ዝንቱ ፤

በዚህ ኢዮቤልዩ በአንዲት ዓመት ደቂቀ ሴት አዩአ ቸው ፤ በደብር ቅዱስ እንደ መላእክት ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እያልን እን ኖራለን ከደቂቀ ቃየል አን ጋባም ብለው ነበርና ስለ ዚህ መላእክት አላቸው ፤

እስመ ሠናያት ለርእይ እማንቱ ፤
እነዚህ ሲያዩዋቸው ደስ ያሰኛሉና ፤
ወነሥአምን ሎቶን ሎሙ አንስትያ እምኩሉን እለ ኃረዩ ፤
ማስት ለ ፲ኮኑአቸው ከሁሉ የመረጧቸውን ወሰዱ ፤
ወወለዳ ሎሙ ውሉደ ፤
ወንዶች ልጆችን ወለዱላቸው ፤
ወእሙንቱ ረዓይት ፤
እነዚህም የተወለዱት ረዓይት ናቸው፤ረዓይት ማለት ኃያላን ማለት ነው ፤ አንድም ከሩቅ የሚያዩ ማለት ነው ፤

፲፤ ወልህቀት ዓመፃ ዲበ ምድር ፤
በደል፣ በዚህ ዓለም በዛች፤
ወኩሉ ዘሥጋ አማሰነት ፍኖታ፤
ሥጋዊ ሁሉ ሥራውን አጠፋ ፤
እምሰብእ እስከ እንስሳ ወእስከ አራዊት ወእስከ አዕዋፍ ፤
ከሰው ጀምሮ እስከ አራዊት፣ እስከ እንስሳ እስከ አዕዋፍ ድረስ ፤
ወእስከ ኩሉ ዘይትሐወስ ፤
በዚህ ዓለም እስከሚመላለሰው ፍጥረት ሁሉ ሥራቸውን አጠፋ ፤
ወኩሎሙ ኀማሽኔ ፍጥረቶሙ ወሥርዐቶሙ ፤
ሁሉም ሥርዓታቸውን አጠፉ ፤
ወአንዙ ይትባልዑ በበይናቲሆሙ ፤
እርስ በርሳቸው ይበላሉ ጀመር ፤ ሦስቱ ሽህ ሁለቱን ሺህ ፤ ሁለቱ ሺህ አንዱን ሽሑንና እንደኛ ያለውን ይበሉ ጀመር ፤
ወዓመፃ ልህቀት በዲበ ምድር ፤
በደል በዚህ ዓለም በዛች ፤
ወኩሉ ሕሊና አእምሮ ለኩሉሙ ዕጓለ እመሕያው ከመዝ እኩይ ኩሉ መዋዕለ ፤
አሁን እንደተናገርሁት ባለ ዘመን ሁሉ ለሰው ሁሉ ክፉ ነገርን የማወቅ ሕሊና ተሰጠው ::

፲፩፤ ወርእያ እግዚአብሔር ለምድር ፤
እግዚአብሔር ምድርን አያት ተመለከታት ፤

ወናሁ ምድር ማለነት ፣
እንሆ ምድር ተበላሽች ጠፋች ፣
ወአማለነት ኩላ ዘሥጋ ሥር ዓታ ፣
ሥጋዊ ደማዊ ፍጥረት ሁሉ ሥርዓቷን አጠፋች ፣
ወአእከዩ ኩሎሙ ቅድመ እግዚ አብሔር ኩሎ ዘሀሎ ውስተ ምድር ፣
ሁሉም በዚህ ዓለም ያለ ውን ክፉውን ሥራ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ሠሩ፣
ወጋቤ እደመስሶ ለሰብእ ፣
ሰውን አጠፋዋለሁ አለ ፣
ወለኩሉ ዘሥጋ በመልዕልተ ገጸ ምድር ዘፈጠረ ፣
በዚህ ዓለም የፈጠረውን ሥጋዊ ደማዊ ሁሉ አጠፋ ዋለሁ አለ ::

፲፪ ፤ ወኖኅ ባሕቲቱ ረከበ ሞገሰ በቅድመ አዕይንቲሁ ለእግዚአ ብሔር ፣
ኖኅ ብቻ በእግዚአብሔር ፊት ባለሟልነትን አገኘ ፣
ወመላእክቲሁ አለ ፈነዎሙ ውስተ ምድር ፣
ወደዚህ ዓለም በላካቸው በመላእክትም ፊት ባለሟ ልነትን አገኘ ፣
ወተምዐ እግዚአብሔር ፈድፋደ ይሥርዎሙ እምኩሉ ሥልጣኖሙ ፣
እግዚአብሔር ከሥልጣና ቸው ይለያቸው ዘንድ ፈጽሞ ተቆጣ ፣
ወይቤለነ ከመ ንእሥሮሙ ውስተ ማዕምቅቲሃ ለምድር በማየ አይኅ ፣
በምድር ጥልቀት ውስጥ እናስራቸው እናጠፋቸው ዘንድ እንዲህ አለን ይላሉ መላእክት ::

፲፫ ፤ ወናሁ እሙንቱ እሡራን በማዕከሎሙ ወብሕትዋን ፣
እንሆ እነዚህም በመካከላ ቸው ታስረው ተግዘዋል ፣
ወዲበ ውሉዶሙ ወጽአ ቃል እምቅድመ ገጹ ከመ ይምሐ ያሙ በሰይፍ ፣
ይምትሮሙ ሲል ነው ፣
በሰይፍ ያጠፋቸው ዘንድ በልጆቻቸው ላይ ቃል ታዘዘ ፣
ወያስስሎሙ እምታሕተ ሰማይ፤
ከሰማይ በታች በዚህ ዓለም ያጠፋቸው ዘንድ ::

፲፬፤ ወይቤ ኢይነብር እንክ መንፈስየ ዲበ ሰብአ ዓለም ፤
እንግዲህ መንፈሰ ረድኤቴ በሰው ላይ አያድርም አለ፤
እስመ እሙንቱኒ ዘሥጋ ፤
እነዚህም ሥጋውያን ናቸውና ፤ አንድም ሥጋዊ ደማዊ ሥራን ይሠራሉና፤
ወይኩን መዋዕሊሆሙ ፻ወ፳ ዓመተ ፤
ዘመናቸውም ፻፳ ዘመን ይሁን አለ ::

፲፭፤ ወፈነወ ሰይፎ ማእ ከሎሙ አሐዱ አሐዱ ከመ ይቅትሉ ቢጸሙ ፤
አንዱም አንዱ ባልጀራውን ይገድል ዘንድ በመካከላቸው ሰይፉን ሰደደ ፤
ወወጠኑ ይቅትሉ ዝንቱ ዘንተ ፤
አንዱ አንዱን ይገድሉ ጀመሩ ፤
እስከ ወድቁ ኩሎሙ በሰይፍ ፤
ሁሉም በሰይፍ እስኪጠፉ ድረስ ፤
ወተደምሰሱ እምነ ምድር ፤
ከዚህ ዓለም እስኪጠፉ ድረስ ፤
ወአበዊሆሙሰ ይኔጽሩ ፤
አባቶቻቸው ግን ይህን ይመለከቱ ነበር ::

፲፮፤ ወእምድኅረዝ ተአሥሩ ውስተ ማዕምቅቲሃ ለምድር እስከ ዕለተ ደይን ዓባይ ፤
ከዚህም በኋላ ቁርጥ ፍርድ እስከሚፈረድበት ቀን ድረስ በጕደጕደ ምድር ውስጥ ታሥረው ተጋዙ ፤
ለከዊነ ኵነኔ ዲበ ኵሎሙ እለ አማሰኑ ፍናዊሆሙ ወምግባሪሆሙ ቅድመ እግዚአብሔር ፤
በእግዚአብሔር ፊት ሥራቸውን በለወጡ ሰዎች ሁሉ መቻያ ለመሆን ፤
ወደምሰለ ኩሉ እመካኖሙ ፤
ሁሉንም ከቦታቸው አጠፋ፤
ወኢተርፈ እምኔሆሙ ወኢአሐዱ ዘኢተኰነነ በኵሉ እከዮሙ ፤
በክፉ ሥራቸው ከነዚህ ያልተፈረደበት አንድ ሰው ስንኳ የለም ::

፲፯፤ ወገብረ ለኵሉ ግብሩ ፍጥረተ ሐዳሰ ወጻድቀተ ፤
ለፍጥረቱ ሁሉ ደግ እውነተኛ የሚሆን ኖኅን መረጠ፤

ከመ ኢየአብሱ በኵሉ ፍጥረ
ቶሙ እስከ ለዓለም ፤
እስከ ዘለዓለም በባሕር
ያቸው እንዳይበድሉ ፤
ወይጸድቅ ኵሉ በበትዝምዱ
ኵሉ መዋዕለ ፤
ሰው ሁሉ በሥራው በየ
ወገኑ በዘመኑ ይከብራል ::

፲፮፤ ወኵነኔ ኵሎሙ ተሠርዐ
ወተጽሕፈ ውስተ ጽላተ ሰማይ፤
የሁሉም ሥርዓታቸው በሰ
ሌዳ ሰማይ ፤ አንድም
በመላእክት ልቡና ተጽፎ
አል ፤
ወአልቦ ዓመፃ ፤
የማይሠረይ ኃጢአት የለም፤
አንድም ያልተጻፈ ኃጢአት
የለም ፤
ወኵሎሙ አለ ይትዓደዉ
እምፍኖቶሙ ለእንተ ተሠ
ርዐት ሎሙ ከመ ይሑሩ ባቲ
ውስተ እኪት ፤
ይኖሩባት ዘንድ ከተሠራ
ላቸው ሥርዐት የወጡ ከሕ
ጋቸው ወደ ኃጢአት ተገር
ኝተው ተጨልጠው የሔዱ
ትም ሁሉ ተጻፉ ፤

፲፱፤ ወለእመ ኢሖሩ ባቲ ፤
በተሠራላቸው ጸንተው ባይ
ኖሩ ፤
ተጽሕፈ ኵነኔ ለኵሉ ፍጥረት
ወለኵሉ ትዝምድ ፤
በሰውም በእንስሳም ወገን
ሁሉ መቻያ ሊሆን ተጽ
ፎአል ፤
ወአልቦ ምንትኒ ዘበሰማይ ወዘ
በምድር ፤
በሰማይ በምድርም ቢሆን
የተሠራው ኃጢአት የሚሠ
ወር የለም ፤
ወውስተ ብርሃን ወውስተ ጽል
መት ፤
በጨለማ በብርሃንም
ቢሆን ፤
ወውስተ ሲኦል ወውስተ ቀላይ፤
በሲኦልም በጥልቅም ውስጥ
ከሚሠራው ኃጢአት ሁሉ
የሚሠወር የለም ፤
ወውስተ መጽልም ፤
በዱር በጨለማ ፤ አንድም
በዋሻ ከሚሠራው ኃጢአት
ሁሉ የሚሠወር የለም ::

፳፤ ወኵሉ ኵነኔሆሙ ስሩዕ
ወጽሑፍ ወቅሩጽ ፤
ፍዳቸው ሁሉ ተጽፏል
ተቀርጿል ፤

በእንተ ኵሉ ለዓቢይኒ በከመ ዕበዩ ፤
ስለ ኃጢአታቸው የታላቁ እንደታላቅነቱ ፤
ወለንዑስኒ በከመ ንዕሱ ፤
የታናሹም እንደታናሽነቱ ፍዳቸው ተጽፏል፤ አንድም የብዙው እንደብዛቱ የጥቂቱ እንደ ጥቂትነቱ ፍዳቸው ተጽፏል ፤
ወለለፀ በከመ ፍኖቱ ይኴንኖ ፤
ለአንዱም ባንዱም እንደ ኃጢአቱ ይፈርድበታል ::

፳፭፤ ወኢኮነ ውእቱ ዘይነሥእ ገጸ ፤
እሱ የሰው ፊት አይቶ የሚአደላ አይደለም ፤
ወኢኮነ ውእቱ ዘይነሥእ ሕልያነ አመ ይቤ እገብር ኵነኔ ለለአሐዱ ፤
በአንዱም ለአንዱም ልፍረድ ባለ ጊዜ መማለጃ የሚቀበል አይደለም ፤
ወለለፀዱ እመ ወሀበ ኵሎ ዘውስተ ምድር ፤
እግዚአብሔር በዚህ ዓለም ያለውን ገንዘብ ሁሉ ለአንድ ሰው ቢሰጥ ፤
ኢይነሥእ ገጸ ፤
ፊት አይቶ አያደላም ፤
ወኢይትሜጠ እምኔሁ ፤
ከሱ ገንዘብ አይቀበልም ፤
እስመ መኰንነ ጽድቅ ውእቱ ፤
የእውነት ዳኛ ፈታሒ በጽድቅ ኰናኒ በርትዕ ነውና::

፳፮፤ ወዲበ ደቂቀ እስራኤል ተጽሕፈ ወተሠርዐ ፤
በእስራኤል ልጆች ላይ ይህ ሥርዓት ሆኖ ተጽፏል ፤
እመ ተመይጡ ኀቤሁ በጽድቅ የኀድግ ኵሎ አበሳሆሙ ፤
በእውነት ወደሱ ከተመለሱ በደላቸውን ሁሉ ይቅር ይላቸዋል ፤
ወይሠሪ ኵሎ ኀጢአቶሙ ፤
ጥቃቅኑን ኃጢአታቸውንም ያስተሠርይላቸዋል ::

፳፯፤ ተጽሕፈ ወተሠርዐ ይት መሀሩ ኵሉ እለ ተመይጡ እምኵሉ ጌጋዮሙ ምዕረ ለለዓመት ፤

ከበደላቸው የተመለሱ ሁሉ በዓመት በዓመት አንድ ቀን ይማሩ ዘንድ ተጽፏል ታዟል ፤

ወዲበ ኵሎሙ እለ አማሰኑ ፍናዊሆሙ ወምክሮሙ ፤
ዲበ ቀሪ ነው ፤ ምክራቸውን ሥራቸውን ባጠፉ በለወጡ ሰዎች ታዟል ፤
እምቅድመ አይኅ ፤
ኢኃፍረ ገጸሙ ይላል ከማየ አይኅ አስቀድሞ ፊታቸው በመከራ አላፈረም ::

፳፬፤ ኢተንሥአ ገጸሙ ዘእንበለ ኖኅ ባሕቲቱ ፤
ከኖኅ ብቻ በቀር ፤ አንድም ኢተንሥአ ፤ ገጸሙ ይላል እነሱ ባለሚልነትን አላገኙም ፤
እስመ ተንሥአ ገጹ በእንተ ውሉዱ እለ አድኃኖሙ እምነ ማየ አይኅ በእንቲአሁ ፤
በሱ ምክንያት ከማየ አይኅ ስለአዳናቸው በልጆቹ ባለሚልነት ተገኘ እንጂ ፤
አንድም እርሱ በባለሚልነት ተገኝቶአልና እነርሱ ባለሚልነትን አላገኙም ፤
እስመ ጻድቅት ይእቲ ልቡ በኵሉ ፍናዊሁ ፤
ልቡ በሚሠራው ሥራ ሁሉ እውነተኛ ናትና ፤
በከመ እዙዝ በእንቲአሁ ፤
ለሱ ስለሱ እንደታዘዘ መጠን ፤
ወኢተአደወ እምኵሉ ዘሥሩዕ ሎቱ ፤
ከታዘዘለት ሥርዐት ሁሉ አልወጣም ::

፳፭፤ ወይቤ እግዚአብሔር ይደምስስ ኵሉ ዘዲበ የብስ እምሰብእ ወእስከ እንስሳ ፤
እግዚአብሔርም በዚህ ዓለም ያለው ሁሉ ከሰው ጀምሮ እስከ እንስሳ ድረስ ይጥፋ አለ ፤
እስከ አራዊት ወእስከ አዕዋፍ ፤
ከአእዋፍ እስከ አራዊት ድረስ ይጥፋ አለ ፤
ወእስከ ዘይትሐወስ ዲበ ምድር፤
በዚህ ዓለም እስከ ሚመላለስ ለስ ፍጥረት ሁሉ ይጥፋ አለ ::

፳፮፤ ወአዘዞ ሎቱ ለኖኅ ይግበር ታቦት ፤
ኖኅን መርከብ ያበጅ ዘንድ አዘዘው ፤
ከመ ያድኅኖ እምነ ማየ አይኅ፤

ከማየ አይኅ ከጥፋት ውሀ ያድነው ዘንድ ከማየ አይኅ በሚድን ገንዘብ መርከብ ይሠራ ዘንድ አዘዘው ፤

፳፯፤ ወገብረ ኖኅ ታቦተ ለዅሉ፤
ኖኅ ለሰውም ለእንስሳም መርከብን ሠራ ፤

በከመ አዘዘ በ፪ቱ ኢዮቤልወ ዓመታት ፤

እንደአዘዘው በሁለተኛው ኢዮቤልዩ ሠራ ፤

በሐምስ ሱባዔ ወበሐምስ ዓመቱ፤

ባምስተኛው ሱባዔ ባምስተኛው ዓመት ለሁሉ መርከብን ሠራ ፤

፳፰፤ ወቦአ በሳድሱ ሎቱ ፤

በስድስተኛው ዘመን ፤

ወበሠርቁ ለካልዕ ወርኅ እስከ አመ አሥሩ ወሰዱሱ ቦአ ፤

ቦአንና ቦአን አንድ ወገን አድርግ ፤ በስድስተኛው ዓመት በሁለተኛው ወር በግንቦት ግንቦት በባተ ባሥራ ስድስት ቀን ፤

ቦአ ውእቱ ፤

እሱ ወደ መርከብ ገባ ፤

ወኵሉ ዘአባዕነ ሎቱ ውስተ ታቦት ፤

አግባ ብለን ያዘዝነውን ሁሉ ወደመርከብ አገባ ::

፳፱፤ ወአፀዎ እግዚአብሔር እንተ አፍአሁ በዐሥሩ ወሰብዑ ምሴት ፤

ባስራ ሰባተኛው ቀን ማታ ጊዜ ፤

ወአሠርቱ ወሠኑዩ ፤

በጨረቃ በአሥራ ሁለት ቀን በግንቦት እግዚአብሔር መርከቡን በውጭ ዘጋው ገጠመው አሪት አሥራ ሁለት ይላል ጳጉሜንን ትቶ ከዚህ ጨምሮ ፤

ወአርኃወ እግዚአብሔር ሰብአተ ምንባኃባኃተ ሰማይ ፤

እግዚአብሔር በጠፈር ሰባት የውሀ መውረጃ ከፈተ ፤

ወአርኃወ አንቅዕተ ቀላይ ዐባይ በሰብዑ አፈው በጕልቊ ፤

በምድር ከሰባት ቦታ ላይ

የምንጩን አፍ ከፍቶታል፤ ሳዊሮስ ፫ ይላል ፤ ከዚህ ሰባት ይላል አይጣላም ? ቢሉ አይጣላም ነገር እንደዚህ ነው፤ሰባት ማለቱ ዐሥሩን አንድ ዐሥሩን አንድ ብሎ ቆጥሮ ነው ።

፴፤ ወአኃዙ ምንባሕባሐት ያውርዱ ማየ እምሰማይ ፶ ኦሞዕለ ወ፶ለያልየ ፤
አርባ መዓልት አርባ ሌሊት የውሀ መውረጃዎች ውሀውን ያወርዱ ጀመር ።

፴፩፤ ወአንቅዕተ ቀላይኒ ያዐርጉ ማያተ እስከ ሰባ መልዐ ኩሉ ዓለም ማየ ፤
ውሃው በዓለሙ ሁሉ እስኪመላ ድረስ የውሃዎች ምንጮች ውሃውን ያፈልቁ ነበር ፤

ወልሕቁ ማያት ዲበ ምድር ፤
ውሆች በምድር ላይ ከፍ ከፍ አሉ ፤

፲ወ፮ተ በዕመት ተለዓለ ማይ ዲበ ኩሉ ደብር ነዋህ ፤
ውሃው በረጅሙ ተራራ ሁሉ ላይ አምስት ክንድ ያህል ከፍ ከፍ አለ ፤

በምን ይታወቃል ? ቢሉ ነቢዩ ባወቀ ተናግሮታል ።

፴፪፤ ወተለዓሉ ማያት ፤
ውሀዎች ከፍ ከፍ አሉ ፤
ሐተታው እንደ አሪት ዘፍ. ምዕ. ፯ ከቁ ፲፭-፲፰ ነው፤

ወተለዐለት ታቦት ዲበ ምድር ፤
መርከብም ከምድር ላይ ከፍ ከፍ አለች ፤

ወታንሶሱ ዲበ ገጸ ማያት ፤
በውሃው ላይ ትመላለስ ነበር ፤

ወሀለዉ ማያት ይቀውሙ ዲበ ገጸ ምድር ፭ አውራኃ ፤
ውሀዎች በምድር ላይ አምስት ወር ጸንተው ነበር ፤

፻ወ፶ ዕለተ ፤.
ይኸውም መቶ አምሳ ቀን ነው ፤

ወሖረት ታቦት ፤
መርከብ ተንሳፈፈች ፤

ወአእረፈትዲበ ርእሰ ሉባር ፭ዱ እምአድባረ አራራት ፤
በአራራት ካሉ ተራራዎች ሉባር ከሚባል ካንድ ተራራ ራስ ላይ አረፈች ።

፴፫ ፤ ወበወርኀ ራብዕ ተፈጽሙ አንቅዕተ ቀላይ ዓባይ ፤
ባራተኛው ወር በሐምሌ ሰፊ የሚሆን የውሀው ምንጭ ተዘጋ ፤
ወምንባሕባሐተ ሰማይኒ ተእኀዝ ፤
በሰማይ ያለው የውሀውም መውረጃ ሻሻቴ ተገታ ::

፴፬ ፤ ወበሠርቀ ወርኀ ሳብዕ ተርኀወ ኵሉ አፈወ ማዕምቅተ ምድር ፤
በሰባተኛው ወር በጥቅምት የውሃው መውረጃ ሁሉ ተከፈተ ፤
ወማዕምቅተ ምድር ፤
ጥልቁ መሬት ሁሉ ተከፈተ በፊት የወጣበትን ዘግቶ በሌላ በኩል ቀዶ አውርዶታል ፤
ወአኃዙ ማያት ይረዱ ውስተ ቀላይ ታሕቲት ፤
ውሆች በወንዙ ውስጥ ወደታች ይወርዱ ጀመር::

ምዕራፍ ፮

፩ ፤ ወበሠርቀ ወርኀ ዐሥር አስተርአዩ አርእስተ አድባር ፤
በዐሥረኛው ወር በጥር መባቻ ፤ የቀርዱ የዓራራት ራስ ታየ ፤
ወበሠርቀ ወርኀ ቀዳሚ አስተርአየት ምድር ጥቀ ፤
በሚያዝያ መባቻ ምድር ፈጽማ ታየች ተገለጸች ፤
ወነጽፉ ማያት እመልዕልተ ምድር ፤
ውሆች ከዚህ ዓለም ደረቁ፤
በሱባዔ ሐምስ በሳብዕ ዓመቱ ሎቱ ፤
አምስተኛው ሱባዔ ሲፈጸም በሺተኛው ዓመት ደረቁ ፤
ወአመ ዐሡር ወሰቡዕ ዕለት በካልዕ ወርኀ የብሰት ምድር ፤
በሁለተኛው ወር በግንቦት በዐሥራ ሰባት ቀን ምድር ደረቅ ሆነች ::

፪ ፤ ወአመ ፳ወ፯ ሎቱ አርኃዋ ለታቦት በአራራት ዘነበረት ፤
በሃያ ሰባተኛው ቀን መርከ ቢቱን ከፈታት ፤
ወአውጽአ ወፈነወ እምውስቴታ አራዊተ ወአዕዋፈ ወዘይትሐ ወስ ፤
አራዊትን አዕዋፍን ፤

የሚመላለሱትን ፍጥረት ሁሉ ከውስጡ አስወጥቶ ሰደደ አሰናበተ ፤
ወአመ ሠርቁ ለወርኀ ሣልስ ፤
በሦስተኛው ወር የሰኔ መባቻ ፤
ወጽአ ኖኅ እምነ ታቦት ፤
ኖኅ ከመርከብ ወጣ ፤
ወሐነፀ ምሥዋዐ ውስተ ዝንቋ ደብር ፤
በዚህ ተራራ ላይ መሠዊያን ሠራ ፤ ወአስተርአየ ዲበ ምድር ፤ በምድርም ላይ ታየ ፤
ወነሥአ መሐስዓ ጠሊ ፤
አንድ የፍየል ጠቦት አመጣ ፤
ወአስተሥረየ በደሙ በእንተ ኩሉ አበሳ ምድር ፤
በምድር ስለ ተሠራው ኃጢአት ሁሉ በደሙ አነጻ፤
እስመ ተደምሰሰ ኩሉ ዘሀሎ ውስቴታ ፤
በምድር ያለው ፍጥረት ሁሉ ጠፍቷልና ፤
ዘእንበለ ዘሀለዉ ምስለ ኖኅ ውስተ ታቦት ፤
ከኖኅ ጋራ በመርከብ ካሉት በቀር በዓለም ያለው ሁሉ ጠፍቷልና ::

፫፤ ወአዕረገ ስብሐ ዲበ ምሥዋዕ ፤
ስቡን ከመሠዊያው ላይ አወጣው ፤
ወነሥአ ላህመ ወበሐኩ ወበግዐ ወአጣሌ ወዔወ ፤
የላሙን ፤ የበጉን ሙክት ፍየሉን ጨውን አመጣ ፤
ወመንጪጠ ፤
ዋኖስን ፤
ወዕጕለ ርግብ ፤
የርግቡን ግልገል አመጣ ፤
ወአዕረገ ጽንሐሐ ውስተ ምሥዋዕ ፤
ስቡን ከመሠዊያው ላይ አቀረበ ፤
ወይሠውጥ ላዕሌሆን መሥዋዕተ ልውሰ በቅብዕ ፤
በዘይት የተለወሰውን መሥዋዕቱን በዚያ ላይ ጨመረ::

፬፤ ወነዝሐ ደመ ፤
ደሙን ረጨ ፤
ወወደየ ላዕለ ኩሉ ስሒን ፤
በመሥዋዕቱ ላይ ቁንዶ በርበሬውን ጨመረ ፤

ወአዕረገ መዓዛ ሠናየ ዘይሠምር ቅድመ እግዚአብሔር ፤
እግዚአብሔር ወዶ የሚቀበለው በጐ መዓዛ ያለውን መሥዋዕት አቀረበ ::

፫፤ ወአዜነወ እግዚአብሔር መዓዛ ሠናየ ፤
ተወክፈ ሲል ነው ፤
እግዚአብሔር በጎ መዓዛ አድርጎ ተቀበለለት ፤
ወተካየደ ምስሌሁ ኪዳነ ከመ ኢይኩን ማየ አይኅ ዘይማስን ምድረ ፤
ሀገሩን ሁሉ የሚያጠፋ ማየ አይኅ እንዳይወርድ ከኖኅ ጋራ መሐላን ተማማለ ፤
ኵሉ መዋዕለ ምድር ዘርዕ ማዕረር አይነትግ ፤
ምድር ጸንታ በኖረችበት ዘመን ሁሉ ዘር መከር አይቀርም ፤ አንድም አይቅር ፤
ደደከ ፤
ደጋ ፤
ወመርቁ ፤
ቄላ ፤
ሐጋይ ወክረምት ፤
ክረምትና በጋ ፤
መዓልት ወሌሊት ፤
መዓልትና ሌሊት ፤
ኢይወልጡ ሥርዐቶሙ ፤
ሥርዓታቸውን አይለውጡም ፤ አንድም እንዳይለውጡ ተማማለ ፤
ወኢያንትጉ ለዓለም ፤
ለዘላለሙ ሥርዐታቸውን እንዳያጐድሉ ::

ጉባዔ

፮፤ ወአንትሙኒ ለሐቁ ፤
እናንተም እደጉ ብዙ ፤
ወተባዝኑ ዲበ ምድር ፤
በዚህ ዓለምም ብዙ የብዙ ብዙ ሁኑ ፤
ወብዝኑ ላዕሌሃ ፤
በእስዋ ላይ ብዙ ፤
ወኩኑ ለበረከት ፤
ለበረከት ሁኑ ፤
ማእከለ ፍርሃትክሙ ወረዓድ ክሙ እሁብ ዲበ ኵሉ ዘውስተ ምድር ወዘውስተ ባሕር ፤
በፍርሃታችሁ በረዓድአችሁ አሕዛብን አመጣለሁ አለ ፍርሃታችሁን
እንቅጥቅጣችሁን ለአሕዛብ አሰጣለሁ እንዲፈሯችሁ አደርጋለሁ አለ::

፯፤ ወናሁ ወሀብኩክሙ ኵሉ አራዊተ ወኵሉ እንስሳ ፤
እንስሳትን አራዊትን ምግብ ሊሆኗችሁ ሰጠኋችሁ ፤

ወኵሉ ዘይሠርር ፤
የሚበረውን ቆቁን ዝርግራ ውን ፤
ወኵሉ ዘይትሐወስ ውስተ ምድር ወውስተ ማያት ፤
በባሕር ውስጥ በምድር የሚመላለሰውን ሁሉ ፤
ወዓሣተ ኵሉ ለሲሲት ከመ ሐመልማለ ሣዕር ፤
ዓሣውን ሁሉ እንደ እኅል ምግብ ሊሆኑአችሁ ሰጠኋ ችሁ ፤
ወወሀብኩክሙ ኵሉ ትብልዐ ፤
ትበሉ ዘንድ ሁሉን ሰጠኋ ችሁ ::

፳፤ ወባሕቱ ሥጋ ዘምስለ መንፈሱ ወምስለ ደም ኢት ብልዐ ፤
መንፈስ ያለውን ደም ብሉ ተረጕመው ነገር ግን ሥጋውን ከደም ጋራ አት ብሉ ፤
እስመ ነፍሰ ኵሉ ዘሥጋ ደም ውእቱ ፤
የነባቢት ነፍስ ማደርያ ነውና ፤
ከመ ኢይትነሠሥ ደመክሙ ውስተ ነፍሳቲክሙ እምውስተ ኵሉ እደ ሰብእ ፤
በሰውነታችሁ ያለ ደምን ከሰው ሁሉ እጅ እንዳል ፈልግ ፤
ወእምደ ሰብእ አኃሥሥ ለደመ ሰብእ ፤
የሰውን ደም ከሰው ሁሉ እጅ እፈልግአለሁ ፤
ዘይክዐ ደመ ሰብእ በእደ ሰብእ ደመ ይትከዓው ፤
የሰውን ደም የሚያፈስ ሰው ደሙ በሰው እጅ ይፈሳል ፤
እስመ በመልክዐ እግዚአብሔር ገብሮሙ ለአዳም ወለብእሲቱ ፤
እግዚአብሔር አዳምንና ሄዋንን በሱ አምሳል ፈጥሯ ቸዋልና ፤
አንትመኒ ለሐቁ ወብዝኁ ውስተ ምድር ፤
እናንተም በዚህ ዓለም ብዙ የብዙ ብዙ ሁኑ አላቸው ::

፳፩፤ ወመሐሉ ኖኅ ወደቂቁ ከመ ኢይብልዐ ኵሉ ደመ ዘበኵሉ ሥጋ ፤
በሥጋ ሁሉ ያለ ደምን እንዳይበሉ ኖኅና ልጆቹ ማሉ ፤

ወተካየደ ኪዳነ ቅድመ እግዚአብሔር አምላክ ዘለዓለም በኵሉ ትውልደ ምድር በዝንቱ ወርኀ ፣

ሰው ሁሉ ጸንቶ በሚኖ ርበት በዚህ ዓለም በእግዚአ ብሔር ፊት መሐላን ተማማለ ::

፲፤ በእንተ ዝንቱ ተናገረክ ትትካየድ ኪዳነ አንተኒ ምስለ ደቂቀ እስራኤል ፤

ስለዚህ ነገር ሙሴ ! አንተም ከእስራኤል ልጆች ጋራ መሐላ ትማማል ዘንድ ተናገረህ ይለዋል መልአከ ገጽ ኖኅን ፤

በዝ ወርኀ በዲበ ደብር ምስለ መሐላ ፤

በሚያዝያ በደብረ ሲና ከመሐላ ጋራ ተናገረህ ፤

ወትነዝኅ ላዕሌሆሙ ደመ በእንተ ኵሉ ነገረ ኪዳን ዘተካየደ እግዚአብሔር ምስሌሆሙ በኵሉ መዋዕል ፤

ባለ በዘመኑ ሁሉ እግዚአ ብሔር ከነዚያ ጋራ ስለ ተማማለው መሐላ ደሙን በዚያ ላይ ትረጫለህ::

፲፩፤ ወጽሕፍት ይእቲ ዛቲ ስምዕ ላዕሌክሙ ከመ ትዕቀብዋ ኵሉ መዋዕለ ፤

ባለ ዘመኗ ሁሉ ትጠብቋት ዘንድ ይህች ሥርዐት በናንተ ላይ ተጽፋለች ፤

ከመ ኢትብልዑ በኵሉ መዋዕል ኵሉ ደመ አራዊት ወአዕዋፍ ፤

በዘመኑ ሁሉ የአራዊትን የአዕዋፍን ደም ሁሉ እንዳ ትበሉ ፤

ኵሉ መዋዕለ ምድር ፤

ምድር ጸንታ በኖረችበት ዘመን ሁሉ እንዳትበሉ ፤

፲፪፤ ወሰብእ ዘበልዐ ደመ አርዌ ወዘእንስሳ ወዘአዕዋፍ በኵሉ መዋዕለ ምድር ፤

ምድር ጸንታ በኖረችበት ዘመን ሁሉ የእንስሳትን የአራዊትን የአዕዋፍን ደም የበላ ሰው ፤

ይሠሮ ውእቱ ወዘርዑ እምድር፤ እሱ ልጆቹ ከዚህ ዓለም ይጥፉ ::

፲፫፤ ወአንተ አዝዞሙ ለደቂቀ እስራኤል ኢይብልዑ ኵሉ ደመ ፤

ደሙን ሁሉ እንዳይበሉ ሙሴ ! የእስራኤልን ልጆች አንተ እዘዛቸው ፤
ከመ የሀሉ ስሞሙ ፤ ወዘርዖ ሙኒ ቅድመ እግዚአብሔር አምላክነ ኵሉ መዋዕለ ፤
ስማቸው ጸንቶ ይኖር ዘንድ ልጆቻቸውም በፈጣሪ ያችን በእግዚአብሔር ፊት ጸንተው ብዙ ዘመን ይኖሩ ዘንድ ::

፲፬ ፤ ወአልቦ ለዝ ሕግ ዓቅመ መዋዕል ፤
ለዚህ ሕግ እስከዚህ ዘመን ድረስ ተብሎ የተወሰነ ዘመን የለውም ፤
እስመ ሕግ ዘለዓለም ውእቱ ይዕቀብዎ ለኵሉ ትውልድ ፤
ይህ ሥርዐት የዘለዓለም ነውና ለልጅ ልጅ ይጠብቁት ፤
ከመ ይኩኑ እንዘ ይትመሐለሉ በእንቲአክሙ በደም በቅድመ ምሥዋዕ ፤
በመሠዊያው ፊት ደሙን በማቅረብ ስለ ናንተ የሚለምኑ ይሆኑ ዘንድ ፤
በኵሉ ዕለት ወዕለተ ነግህ ወሠርክ ያስተሥርዩ በእንቲአሆሙ ወትረ ቅድመ እግዚአብሔር ፤
በየቀኑ ጧትና ማታ ኃጢአታቸውን በእግዚአብሔር ፊት ያስተሠርዩ ዘንድ ፤
ከመ ይዕቀብዎ ፤
ይጠብቁት ዘንድ ፤
ወኢይሠረዉ ፤
እንዳይጠፉ ::

፲፭ ፤ ወወሀቦ ለኖኅ ወለደቂቁ ትእምርተ ኪዳኑ ፤
የቃል ኪዳኑን ምልክት ለኖኅና ለልጆቹ ሰጣቸው ፤
ከመ ኢይኩን እንከ አይኅ ዳግመ ዲበ ምድር ፤
ማየ አይኅ ዳግመኛ በምድር ላይ አንዳይመጣ ፤
ቀስቶ ወሀበ ውስተ ደመና ለትእምርተ ኪዳን ዘለዓለም ፤
የዘለዓለም መሐላ ምልክት ሊሆን ብርሃኑን በደመና ስሎ አሳየው ፤
ከመ ኢይኩን እንከ ዳግመ ማየ አይኅ ዲበ ምድር ፤
ዳግመኛ ማየ አይኅ ፤

በምድር ላይ እንዳይወርድ፤
ለአማስናታ ኵሉ መዋዕለ ዲበ ምድር ፤
ምድር ጸንታ በኖረችበት ዘመን ሁሉ እንዳይወርድ።

፲፮፤ ወበእንተዝ ተሠርዐ ወተ ጽሕፈ ውስተ ጽላተ ሰማይ ፤
ስለዚህ ነገር በመላእክት ልቡና ተጻፈ ፤
ከመ ይኩኑ ገበርተ በዓል ዘሱባዔያት በዝወርኀ ምዕረ ለለዓመት ለሐዲስ ኪዳን በኵሉ ዓም ወዓመት ፤
መሐላን ለማጽናት በዓ መት በዓመት አንድ ጊዜ በዚህ በሚያዝያ በሱባኤ የሚቆጠር በሱባኤ ውስጥ ያለ በዓልን የሚያደርጉ ይሆኑ ዘንድ ፤

፲፯፤ ወኮነት ኵላ ዛቲ በዓል እንዘ ትትገበር በሰማይ እምዕ ለተ ፍጥረት እስከ መዋዕለ ኖኅ፤
ከዕለተ ፍጥረት ጀምሮ እስከ ኖኅ ድረስ ይህች በዓል በመላእክት ዘንድ ፤
ስትሠራ ኖረች ማለት ነው፤ አሁን መላእክት ሠርተዋት አይደለም በዓልነቷን ስለአ ወቁ ነው እንጂ ፤
፰ወ፯ቱ ኢዮቤልው ወሱባዔ ዓመት ፎቱ ፤
ይኸውም ሃያ ሰባት ኢዮቤ ልዩ አምስት የዘመን ሱባዔ ነው ፤
ወአቀብዋ ኖኅ ወደቂቁ ሰብአተ ኢዮቤልወ ወሱባዔ ዓመታት አሐተ እስከ አመ ዕለተ ሞቱ ለኖኅ ፤
ኖኅ እስኪሞት ድረስ አንዲቱን የዘመን ሱባዔ ፯ቱን ኢዮቤልዩ ጠብቀው በዓል ያደርጉ ነበር ፤
ኢዮቤልዩ አርባ ዘጠኝ ዘመን ነው ስድስቱን ዘመን ሲሰሩ ኑረው በሰባተኛው ዘመን ያርፋሉ ፤ እንዲህ ሲያደርጉ እስከ አርባ ዘጠኝ ዘመን ይኖራሉ፤ዘጠነኛይቱ ዘመን የዘመን መለወጫ ቸው ናት፤ አሁን ዛሬ እኛ የዘመን መለወጫ ነው ብለን የመስከረም ቅዱስ ዮሐንስን በዓል አድርገን

አክብረን እንደምንውል እነ ሱም በዓል አድርገው አክብ ረው ይቀመጣሉ ፤

፱ ሃምሳኛዪቱንም ዘመን በዓለ ተሐውሶ አድርገው አክብረው ያርፉባታል ፤ ከዚያ በኋላ ሥራ ይጀም ራሉ ፤ እኛ በዓመት በዓል በነጋው በዓለ ተሐውሶ አድርገን አርፈን እንድን ውል፤ኢዮቤልዩ ማለት የዘ መን ቁጥር ማለት ነው ::

፲፤ ወእምድኅረ ሞቱ ለኖኅ አማለኑ ውሉዱ እስከ አመ መዋዕለ አብርሃም ፤
ኖኅ ከሞተ ጀምሮ ልጆቹ እስከ አብርሃም ዘመን ድረስ ሥርዓቱን አጠፉ ፡
ወይበልዑ ደመ ፤
ብርንዶውንም በሉ ፤
ወአብርሃም ባሕቲቱ ዐቀበ ሕገ ፤
አብርሃም ብቻ ሕግን ጠበ ቃት ፤
ወይስሐቅ ወያዕቆብ ዐቀብዋ እስከ መዋዕሊከ ፤
ይስሐቅ ያዕቆብ እስከ አንተ ዘመን ድረስ ጠበቁት ፤
ወበመዋዕሊከ ረስኡ ውሉደ እስራኤል እስከ አመ ሐደስ ክምሙ በንበ ዝ ደብር ፤
በደብረ ሲና በረድኤት እስ ከአድሳቸው ድረስ የእስራ ኤል ልጆች በዘመንህ ሕጉን ዘነጉ ፤ ረስዑ ይላል መልአከ ገጽ ::

፲፬ ፤ ወአንተሂ አዝዞሙ ለደቂቀ እስራኤል ፤
ሙሴ!አንተም የእስራኤልን ልጆች እዘዛቸው ፤
ወይዕቀብዋ ለዛቲ በዓል በኵሉ ትዝምዶሙ ለትእዛዝ ሎሙ ፤
ይቺንም በዓል በወገኖቻ ቸው ሁሉ ሥርዓት ልትሆ ናቸው ይጠብቋት ፤
ዕለተ አሐተ በዓመት በዝ ወርኅ ይግበሩ በዓለ ዛቲ ፤
በሚያዝያ በዓል ያደርጉባት ዘንድ በዓመት አንድ ቀን ያክብሩ ፤
እስመ በዓለ ሱባዔያት ይእቲ ፤
በሱባዔ የምትቆጠር በዓል ናትና ::

፷፤ ወበዓለ ቀዳሚ ፍሬ ይእቲ፡ መጀመሪያ የደረሰውን እህል የሚሰበስቡባት ናትና በዓል አድርገው የሚያከብሯትን በዓለ ሠዊትን ያክብሯት ፤

ክልዔ ዕፅፈት ይእቲ ፤ ይህቺውም ሁለት ወገን ናት ፤

ወለፂቱ ዘመድ ዛቲ በዓል ፤ ይህች በዓል ለሰውና ለመላ እክት ተሠርታለች ፤

በክመ ጽሑፍ ወቅሩጽ በእንቲ አሃ ግብራ ፤

ሕን እንደ ተቀረጸ እንደ ተጻፈ መጠን ይህችም በዓል ልትከብር ሊያከብሯት ለሁለቱ ለሰውና ለመላእክት ተሰጠች ፤

እስመ ጸሐፍኩ ውስተ መጽሐፈ ሕግ ዘቀዳሚ ውስተ ዘጸሐፍኩ ለከ ትግበራ በበጊዜሃ ዕለተ አሐተ ለዓመት ፤

ከዓመት አንድ ቀን በጊዜዋ ጊዜ ታደርጋት ዘንድ አስቀድሜ በጻፍኩልህ ሕግ በተጻፈበት በልቡናህ ጽፌዋ ለሁና ::

፷፩፤ ወቍርባኖሂ ነገርኩከ ከመ ይኩኑ ዝኩራነ ፤ መታሰቢያ ይሆኑ ዘንድ ቍርባኑንም ነገርሁህ ፤

ወይግበርዋ ደቂቀ እስራኤል ውስተ ትዝምዶሙ በዝ ወርኀ አሐተ ዕለተ ለለፅዱ ዓመት ፤ የእስራኤል ልጆች በየወገኖቻቸው በዚህ ዓመት አንድ ቀን በመጀመሪያዋ በሚያዝያ ያክብሯት ::

፷፪፤ ወበሠርቀ ወርኀ ቀዳሚ፤ ሚያዝያ በባተ በመጀመሪያ ፤

ወበሠርቀ ወርኀ ራብዕ ፤ ባራተኛው ወር በሐምሌ ያክብሩ ፤

ወበሠርቀ ወርኀ ሳብዕ ፤ በሰባተኛው ወር በጥቅምት፤

ወበሠርቀ ወርኀ ዐሥር ፤ ባሥረኛው ወር በጥር ፤

ዕለታተ ተዝካር እማንቱ ወዕለታተ ጊዜ እማንቱ ፤

እሊህም የመታሰቢያ ቀን የሚለይባቸው ቀናት ናቸውና ያክብሩ ፤

ውስተ አርባዕቱ መክፈልተ ዓመት ጽሑፋት እማንቱ ፤

እነሱም የተጻፉ የተቆጠሩ ናቸው ፤ አራት ክፍለ ዘመን የተባሉ ሐጋይ ፤ መጻው ፤ ክረምት ፤ ጸደይ ናቸው ፤ ይህ አሥራ ሁለቱ ወር ነው ፤ የአ ሥራ ሁለቱ ወር ዕለታታ ቸው አምስት ጳጉሜን አንድ አንዲቱ በመካከል እየገባች ሦስቱ ወር ዘጠና አንድ ፤ ሦስቱ ወር ዘጠና አንድ ዕለት ነው ፤ ጳጉ ሜን ከሦስቱ ከሦስቱ መካከል ስለገባች ዘጠና አንድ ተባለች፤ አንድ የተባለች እሷ ናት ፤

ወሥሩአት ለሳምን ዓመት ፤

ለዘመንም ምስክር፤ ዳኛ ፤ ዋስ ጠበቃ ሊሆኑ የተሠሩ የተቈጠሩ የተጻፉ ናቸው፤ አለህ እግዚአብሔር ይለ ዋል መልአከ ገጽ ሙሴን ::

፳፫፤ ወኖኅ ሠርየን ሎቶን ሎቱ ለበዓላት ለትውልድ ዘለዓለም ፤ ኖኅም ለዘለዓለም ለልጅ ልጅ ለሚኖሩ ለሱም ሥር ዓት ሊሆነው በዓላትን ሠራቸው ፤

እስከ አመ ኮነ ሎቱ ቦቶን ተዝካር ፤

እነዚህ መታሰቢያ እስኪሆ ኑለት ድረስ ::

፳፬፤ በሠርቀ ወርኅ ቀዳሚ ተብሀለ ይግበር ሎቱ ታቦተ ፤

በመጀመሪያው ወር በሚያ ዝያ ታቦትን ይሠራ ዘንድ ታዘዘ ፤

ወባቲ የብሰት ምድር ፤

በእሷ ምድር ደረቅ ሆነች፤

ወአርኃወ ወርእየ ምድረ ፤

መስኩን ከፍቶ ምድርን አየ ::

፳፭፤ ወበሠርቀ ወርኅ ራብዕ ፤ ባአራተኛው ወር በሐምሌ መባቻ ፤

ተፈጽመ ፤ አንቅዕተ ቀላይ ዓባይ ፤

ሰፊ የሆነ የጥልቁ ምንጭ ተዘጋ ፤

ወምንኅባኃሐተ ሰማይ ተኣኅዘ፤ የሰማዩም ሻሻቴ ተገታ ::

፳፮፤ ወበሠርቀ ወርኅ ሳብዕ ፤ በሰባተኛው ወር በጥቅ ምት፤

ተርጎመ ኩሉ አፈወ ማዕምቅት ዘምድር ፤
በጥልቅ ምድር ያሉ ምንጮች ሁሉ አፋቸው ተከፈተ ፤
ወአኀዙ ማያት ይረዱ ውስተ ቀላያት ታሕቲት ፤
ውሃዎች ከወንዙ ወደታችኛው ጥልቅ ይወርዱ ጀመረ ፊት የወጡበትን ዘግቶ በሌላ ቀደ አውርዶ አቸዋል ::

፳፯፤ ወበሠርቀ ወርኀ ዐሥር፤
በአሥረኛው ወር በጥር ፤
አስተርአዩ አርእስተ አድባር ፤
የተራራዎች ራስ ታዩ ፤
በአሪት ዐሥራ ሁለት ይላል ፤
ወተፈሥሐ ኖኅ ፤
ኖኅም ደስ አለው ፤
ወበእንተዝ ሠርፆን ኪያሆን ሎቱ ለበዓላት ለተዝካር እስከ ለዓለም ፤
ስለዚህ ነገር እስከ ዘለዓለሙ መታሰቢያ ሊሆኑ እነዚህን በዓላት ሠራቸው፤
ከመዝ እማንቱ ሥሩዓት ፤
እነዚህ በዓላት እንደዚህ ተሠርተዋል ፤

ወያዐርግዎን ውስተ ጽላተ ሰማይ ፤
በመላእክት ልቡና ተጽፈ ዋል ::

፳፰፤ ዐሥሩ ወሠላስ ሰንበታት አሐቲ አሐቲ እምኔሆን ፤
ከነዚህ እንዲቱም አንዲቱ አስራ ሦስት ሱባዔ ናቸው፤
እምዛቲ ውስተ ዛቲ ተዝካሮን እምቀዳሚት እስከ ካልዕት ፤
እምዛቲና እምቀዳሚት አንድ ወገን ፤ ከሚያዝያ እስከ ሐምሌ ዘጠና አንድ ቀን ፤
ወእምካልዕት እስከ ሣልሲት ፤
ከሐምሌ እስከ ጥቅምት ዘጠና አንድ ቀን ነው ፤
ወእምሳልሲት እስከ ራብዒት ፤
ከጥቅምት እስከ ጥር ፤
እምራብዒት እስከ ቀዳሚት ፤
ከጥር እስከ ሚያዝያ ድረስ ዘጠና አንድ ቀን ነው ::

፳፱፤ ወይከውና ኩሎን መዋዕል ዘትእዛዛት ፱ወ፪ተ ሰንበታተ መዋዕለ ፤
እነዚህ የታዘዙ ዕለታት ሁሉም ሣምሳ ሁለት የዕለት ሱባዔ ይሆናሉ ፤

ወኵሉ ዓመት ፍጹም ከመዝ ተቀርጸ ወተሠርዐ ውስተ ጽላተ ሰማይ ፤
ፍጹም የሆነ ዓመቱ ሁሉ እንዲህ ተቆጥሮ በመላ እክት ልቡና ታውቋል፤
ወአልቦ ተአድሞ ፩ደ ዓመተ ወዓመ ወዓመተ ፤
ከዓመት እስከ ዓመት አንድ ዓመት ሁለት ዓመት ሦስት ዓመት አንዲት ሳይ ታወቅ የሚቀር የለም ::

፴፤ ወአንተኒ አዝዞሙ ለደቂቀ እስራኤል ይዕቀቡ ዐመታተ በዝ ጕልቍ ፫ተ ፪ተ ፶ ወረቡዐ መዋዕለ ፤
ሙሴ ! አንተም በዚህ ቁጥር ሦስት መቶ ስልሳ አራት ቀን ይጠብቁ ዘንድ የእስራኤልን ልጆች እዘዛቸው ፤
ወይከውን ፍጹመ ዐመተ ፤
ፍጹም ዓመት ይሆናል ፤
ወአማስኑ ጊዜሁ እመዋዕሊሁ ፤
ጊዜውን ዘመኑን አጠፉ ፤
ወእምበዐላቲሁ ፤
በዐሉን አጠፉ ፤
እስመ ኵሉ ይበጽሕ በመ· በከመ ስምዖሙ ፤
እንደምስክርነታቸው ሁሉ በነዚህ ይደረጋልና ፤
ወኢያትርፉ ዕለተ ወኢያማስኑ በዐለ ፤
ቀኑን አያስተላልፉ በዓሉን አይለውጡ ::

፴፩፤ ወለእመ ተዐደዉ ፤
ቀኑንም ቢያስተላልፉ ፤
ወኢገብርዎን በከመ ተአዘዙ ሎቱ፤
እሱ እንዳዘዘ ባያከብሯቸው፤
አሜሃ ኵሎሙ ያማስኑ ጊዜያቲሆሙ ፤
ያንጊዜ ሁሉም ጊዜያቸውን ያጠፋሉ ::
፴፪፤ ወዐመታትኒ ይትሐወሱ ዝ ውስተ ዝ ፤
ዘመኖችም ይፋለሳሉ ማቴ ዎስ ከማርቆስ ፤ ማርቆስ ከማቴዎስ ፤
ወጊዜያትኒ ይማስኑ ፤
ጊዜያትም ይለወጣሉ ፤
ወዓመታትኒ ይትሀወሱ ፤
፬ቱ ክፍለ ዘመንም ከዚህ ወደዚህ ይፋለሳሉ ፤
ወይትዐደው ሥርዓቶሙ ፤
ሥርዓታቸውም ይፋለሳል፤

ወኵሎሙ ውሉደ እስራኤል ይረ
ሥኡ፤

የእስራኤል ልጆች ሁሉ ሥር
ዓታቸውን ይዘነጋሉ።

ወኢይረክቡ ፍኖተ ዓመታት፤

የዘመኑን ቁጥር አያገኙትም፤

ወይረስዑ ሠርቀ ወጊዜ፤

ሠርቀ ወርኀን፤ ጊዜውንም
ይዘነጋሉ፤

ወሰንበተ፤

ሱባዔውን ይዘነጋሉ

ወኵሉ ሥርዓተ ዘዓመታት ይጌ
ግዩ፤

ባራቱ ክፍለ ዘመን የሚሠራ
ውን ሥራ ሁሉ ይስታሉና።

፴፫፤ እስመ አነ አአምር ከመ
ይስሕቱ፤

እንዲስቱ እኔ አውቃለሁና፤

ወእምይእዜ አነ አየድዐከ፤

ከዛሬ ጀምሮ እኔ እነግርህአ
ለሁ፤
ወአኮ ዘእምልብየ፤

የምነግርህም ከልቤ አንቅቼ
አይደለም፤

እስመ ከመዝ መጽሐፍ ጽሑፍ
በቅድሜየ፤

መጽሐፍ በፊቴ እንዲሀ ተጽ
ፏልና እያልኩ እንግርህ
አለሁ።

ወተሠርዐ ውስተ ጽላተ ሰማይ
ኩፋሌሁ ለመዋዕል፤

የዘመኑ አከፋፈል በመላእክት
ልቡና፤ አንድም በሠሌዳ
ሰማይ ተጽፏል ፤

ከመ ኢይርሥዑ በዓላተ ኪዳን፤
ቃል ኪዳን ያለባቸውን በዓ
ላት እንዳይዘነጉ፤

ወኢይሑሩ በበዓላተ አሕዛብ ድኅረ
ስሕተቶሙ፤

ከሳቱ በኋላ ወደ አሕዛብ
በዓል እንዳይሄዱ፤

ወድኅረ ኢያአምሮቶሙ፤

ካለማወቃቸውም በኋላ፤

፴፬፤ ወይከውኑ እለ ያስተሐይጹ
ወርኃ በሥዓቴ ወርኀ፤

ወሩን ከወር በማሳነስ የሚ
መለከቱ ይሆናሉ፤

እስመ ታማስን ይእቲ ጊዜያተ
(ይእቲ ሕፀፀ ወርኀ)

እሷ ጊዜያቱን ትለወጥለ ችና፤

ወትቀድም እምዓመታት ለዓ መት ዓሡረ ዕለተ፤

ከዘመናት ከዓመት ዓመት፤ ዐሥር ቀን ትቀድማለችና።

፴፫፤ በእንተዝ ይመጽኣ ዓመ ታት ሎሙ፤

ስለዚህ ነገር ሥርዓቱን ከለ ወጡ በኋላ ብዙ ዘመኖች ይመጡላቸዋል፤

እንዘ ያመስኑ ወይገብሩ ዕለተ ስምዕ ምንንተ፤

ምስክር የምትሆን ቀንንም የተናቀች ያደርጋሉ ማለት በዓሉን ለውጠው የሥራ ቀን ያደርጋሉ፤

ወዕለተ ርኵስተ በዓለ፤

በዓሊቱንም የረከሰች ቀን ያደርጋሉ፤

ወኵሉ ይዴምሩ

ንጹሑን ቀን ሁሉ ይቀላቅ ላሉ፤

ወመዋዕለ ዘቅዱሳት ርኵሰ

በዓላቱንም ሥራ ያደርጋሉ፤

ወዕለተ ርኵስተ፤ ላዕለ ቅድ ሳት፤

ሥራውን በዓል ያደርግ አሉ፤

እስመ ይስሕቱ አውራኃ፤

ዓሥራሁለቱን ወር፤

ወሰንበታተ፤

ሱባዔውን፤

ወበዓላተ፤

በዓለ መፀለትን በዓለ ሠዊ ትን በዓለ ፋሲካን፤

ወኢዮቤላተ፤

አርባ ዘጠኙን ዘመን ሁሉ ይስታሉና።

፴፮፤ በእንተዝ አነ እኤዝዘከ ፤

ስለዚህ ነገር እኔ አዝሀአ ለሁ፤

ወአስምዕ ለከ ከመ ታስምዕ ሎሙ፤

ታዳኝባቸው ዘንድ አስተም ርሀለሁ፤

እስመ እምድኅረ ሞትከ ያማስኑ ውሉድከ፤

አንተ ከሞትክ በኋላ ልጆችህ ይለውጡታልና፤

ከመ ኢይግበሩ ይተ ያተ ወጌወረ ቡዓ ባሕቲቶን፤

ዓመቱን ሦስት መቶ ስልሳ አራት ብቻ እንዳያደርጉ አዳኝ ባቸዋለሁ።

፴፯፤ በእንተዝ ይስሕቱ ሠርቀ ወሰንበተ፤

ስለዚህ ነገር ሠርቀ ወርኀንና ሱባዔውን

ወጊዜ፤

ጊዜውን፤

ወበዓላተ፤

በዓላቱን ይለውጣሉ፤

ወይበልዑ ኵሉ ደመ ምስለ ኵሉ ዘሥጋ፤

ደሙን ከሥጋ ጋራ ይበላሉ።

ምዕራፍ ፳

፩፤ ወበሱባዔ ሳብዕ፡ በቀዳሚ ዓመቱ ለዝ ኢዮቤልው፤

በሰባተኛው ሱባዔ በዚህ ኢዮቤልዩ በመጀመሪያው ዓመት፤

ተክለ ወይነ ኖኅ ኀበ ደብር እንተ ዲቤሁ አዕረፈት ታቦት፤

ኖኅ መርከቢቱ ካረፈችበት ተራራ ላይ ወይንን ተከለ፤

ዘስሙ ሉባር እምአድባረ አራራት ፤

በአራራት ካሉ ተራሮች ስሙ ሉባር በሚባል ተራራ ላይ ወይንን ተከለ።

፪፤ ወገብረ ፍሬ በራብዕ ዓመት ፤

በአራተኛው ዘመን አፈራ፤

ወዓቀበ ፍሬሁ በውእቱ ዓመት፤

ወቀሠመ በወርኀ ሳብዕ፤

በዚህ ዓመት በሰባተኛው ወር በጥቅምት ፍሬውን ለቀመ፤

ወገብረ እምውስቴቱ ወይነ፤

ከዚህ ጠጅ አድርጎ፤

ወወደዮ ውስተ ንዋይ ወዐቀቦ እስከ ዓመት ሐምስ፤

በዕቃ አድርጎ እስከ አምስት ዓመት ጠበቀው፤

እስከ ዕለት ቀዳሚት፤

እስከ መጀመሪያይቱ ቀን ድረስ ጠበቀው፤

፫፤ በሠርቀ ወርኀ ቀዳሚት ፤

ከወር የሚቀድም እስከ ሚያ ዝያ መባቻ ድረስ፤

ወገብረ ዛተ ዕለተ በዓለ በፍሥሓ፤

ይህችን ዕለት የሚያዝያን መባቻ ደስ ብሎት አከበራት።

ወገብረ ጽንሐሐ ለእግዚአብሔር።

ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ሠዋ።

ጣዕዋ እምአልሕምት ፩ደ።

ከላሞች ወገን የሚሆን አንድ ወይፈን፣

ወበሐሎ ፩ደ።

አንድ የበግ ሙክትን።

ወአባግዐ ዘዘዓመት ሰብዓተ፣

ሰባት ዓመት የሆናቸው ሰባት በጎችን፣

ወመሐስዐ ጠሊ ፩ደ፣

አንድ የፍየል ጠቦትን እነዚህን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አቀረበ።

ከመ ያስተሥሪ ሎቱ ለርእሱ።

ለራሱ ያስተሠርይበት ዘንድ።

፬። ወበእንተ ውሉዱ።

ስለ ልጆቹ ያስተሠርይበት ዘንድ።

ወገብረ መሐስዐ ቅድመ፣

ጠቦቱን አስቀድሞ ሠዋ።

ወአንበረ እምነ ደሙ ዲበ ሥጋ ዘምሥዋዕ ዘገብረ፣

በሠራው መሠዊያ ካለ ሥጋ ላይ ደሙን አደረገ።

ወዙሉ ስብሐ አዕረገ ውስተ ምሥዋዕ ዘጎበ ገብረ ጽንሐሐ።

ስቡን ሁሉ ምሥዋዕቱን ከአ ደረገበት መሠዊያ ላይ አወ ጣው።

ወላሕመ ወበሐሎ ወአባግዓ አዕ ረገ ወዙሉ ሥጋሆሙ ዲበ ምሥ ዋዕ አንበረ።

ላሙን በጉን በሠዋበት መሠ ዊያ ላይ ሥጋቸውን አሳረገ።

ወአንበረ ዙሉ ሥጋሆሙ ልውሰ በቅብዕ ላዕሌሆሙ ።

በዘይት የተለወሰውን መሥ ዋዕቱን ሁሉ በነዚያ ላይ አኖረ።

፭። ወእምዝ ነዝሐ ወይነ ውስተ እሳት ዘዲበ ምሥዋዕ።

ከዚህ በኋላ ወይኑን በመሠ ዊያው ላይ ካለ እሳት ላይ ረጨው።

አቅደመ ወአንበረ ስሒነ ዲበ ምሥ ዋዕ።

አስቀድሞ ዕጣኑን ከመሠዊያው ላይ አደረገ፤

ወአዕረገ መዓዛ ሠናየ ዘይሠምር እግዚአብሔር፤

እግዚአብሔር የሚወደው በጎ መዓዛ አድርጎ አቀረበው፤

ወዐርገ ቅድመ እግዜአብሔር አምላኩ፣

ከፈጣሪው ከእግዚአብሔር ፊት ደረሰ፣

ወተፈሥሐ፣

ኖኅ ደስ አለው፤

ወሰትየ እምዝንቱ ወይን ውእቱ ወውሉዱ በፍሥሐ ፤

እሱም ልጆቹም ከዚህ ወይን ጠጥተው ደስ አለው።

፮፤ ወኮነ ምሴተ ወቦአ ውስተ ሰቀላሁ፤

በመሸም ጊዜ ወደቤቱ ገባ ፤

ወሰከበ ስኩረ ወኖመ ፤

ሰክሮ ፈጽሞ ተኛ፤

ወተከሥተ በውስተ ሰቀላሁ እንዘ ይነውም፤

በቤቱ ተኝቶ ሳለ ተራቆተ።

፯፤ ወርእዮ ካም ዕራቆ ለኖኅ አቡሁ ፤

ካምም የአባቱ የኖኅን መራቆት አይቶ፤

ወወጽአ ወነገረ ለ፪ቱ አኀዊሁ በአፍኣ፤

ወጥቶ በውጭ ላሉ ለሁለቱ ወንድሞቹ ነገራቸው።

፰፤ ወነሥአ ሴም ልብሶ፤

ሴም ልብሱን አነሣ፣

ወተንሥአ ውእቱ ወያፌት ፤ እሱና ያፌት ተነሱ፤

ወአንበሩ ልብሰ ዲበ መታክፍቲሆሙ፤

ልብሳቸውን በትከሻቸው ላይ አደረጉ፣

ወገጸሙ ኢ፫ብኡ ድኅሪተ፤

ፊታቸውን ወደ ኋላቸው መልሰው፤

ወከደኑ ኃፍረተ አቡሆሙ፤

ያባታቸውን እርቃን አለበሱ።

፱፤ ወነቂሖ ኖኅ እምንዋሙ አእመረ ኩሎ ዘገብረ ላዕሌሁ ወልዱ ዘይንዕስ ፤

ኖኅም ከእንቅልፉ በነቃ ጊዜ ትንሹ ልጁ በሱ ላይ ያደረገውን አወቀ።

ወረገሞ ለወልዱ።

ልጁን ረገመው።

ወይቤሎ ርጉም ከነአን።

ከነአን ርጉም ነው አለ።

ቅኑየ ገብረ ይኩን ለአኀዊሁ።

ለወንድሞቹ ተገዥ ባሪያ ይሁን አለ።

፲። ወባረከ ለሴም።

ሴምን መረቀው።

ወይቤ ይትባረክ እግዚአብሔር አም ላኩ ለሴም።

የሴም ፈጣሪ እግዚአብሔር ይመስገን አለ።

ወያስፍሕ እግዚአብሔር ምድሮ ለያፌት።

ለያፌት እግዚአብሔር አገሩን ያስፋለት።

ወይኅድር እግዚአብሔር ውስተ ማኅደሩ ለሴም።

እግዚአብሔር ከሴም በተወለደ አብርሃም ይደር።

አንድም እግዚአብሔር ከአብርሃም በተወለደች በማኅፀነ ማርያም ይደር። ለይኅድር እግዚአብሔር ውስተ ሐይመቱ ለሴም ከመ ትኩን ክፍሉ። ኢየሩሳሌም ይላል አብነት።

ወይኩን ከነዓን ገብሮ።

ከነዓን ባሪያው ይሁን።

፲፩። ወአእመረ ካም ከመ ረገሞ አቡሁ ለወልዱ ዘይንዕስ።

ካም ታናሹ ልጁን አባቱ እን ደረገመው አወቀ።

ወሐሱም ሎቱ።

ለሱም ክፉ ነገር ሆነበት።

እስመ ረገሞ ለወልዱ።

ልጁን ረግሞታልና።

ወተፈልጠ እምአቡሁ ውእቱ።

እሱ ከአባቱ ተለየ።

ወውሉዱ ምስሌሁ።

ልጆቹም ከሱ ጋራ ተለዩ።

ኩሳ ወሜስጥሮም ወፉድ ወከነ አን።

እነዚህም የካም ልጆች ሜስጥ

ሮም ኵሽ ከነዓንና ፉድ ናቸው፤

ወሐነፀ ሎቱ ውእቱኒ ሀገረ፤ እሱም ኖኅ ሀገር አቀና፤

ወጸውአ ስሞ በስመ ብእሲቱ አኤ ልታማክ፤

የአገሪቱንም ስም በሚስቱ ስም አኤልታማክ ብሎ ጠራ።

፲፪፤ ወርእየ ያፌት ወቀንዐ በእ ኁሁ፤

ያፌትም አይቶ በወንድሙ ቀና፤

ወሐነፀ ሎቱ ውእቱኒ ሀገረ፤

እሱም ለራሱ አገር አቀና፤

ወጸውአ ስሞ በስመ ብእሲቱ አዳ ታኔሴስ፡

በሚስቱ ስም አገሪቱን አዳ ታኔሴስ አላት።

፲፫፤ ወሴምሰ ነበረ ምስለ አቡሁ ኖኅ፤

ሴም ግን ካባቱ ኖኅ ጋር ተቀመጠ፤

ወሐነፀ ሀገረ በእደ አቡሁ ኀበ ደብር፤

በአባቱም ቃል በተራራው ላይ አገር አቀና፤

ወጸውአ ስማ ውእቱኒ በስመ ብእ ሲቱ ሴዶቃቴልባብ፤

እሱም ስሟን በሚስቱ ስም ሴዶቃቴልባብ አላት።

፲፬፤ ናሁ አህጉር እላንቱ ሠላስ፤

እንሆ እኒህ ሀገሮች ሦስት ናቸው፤

ቅሩበ ሎባር ደብር፤

ሎባር በሚባል ተራራ አጠገብ፤

ሴዶቁቴልባብ ቅድመ ገጸ ደብር በጽባሒሁ፤

የሴም ነው፤ ሴዶቁተልባብ በሎባር አንባር በምሥራቁ በኩል ናት፤

ወኢልታማኡክ ገጸ ሰሚኑ፤

ገጸ ሰሚኑ የካም ነው፤ ኢል ታማኡክ በሰሜኑ በኩል ናት፤

አዳታኔሴስ መንገለ ባሕር፤

የያፌት ነው፤ ዕጣቸው አይደ ለም፤ በፈቃዳቸው ያቀኑት ነው፤

አዳታኔሴስም በምዕራቡ በኩል ናት።

፲፭፤ ወእሉ ውሉደ ሴም፤

የሴም ልጆች እነዚህ ናቸው፤

ኤላም፣ ወአቡር፣ ወአርፋክስድ፤

ኤላም አቡርና አርፋክስድ ናቸው፤

ዝንቱ ትውልድ እምድኅረ ፪ቱ ዓም ዘአይኅ፤

ይህ ትውልድ ማየ አይኅ ከወጣ ከሁለት ዓመት በኋላ የተደረገ ነው፤

አራም ወልደ ሉድ ወለደ ኢያፌ ትሃ፣

የሉድ ልጅ አራምም ኢያፌትን ወለደ፤

ወኢያፌት ወለደ ጎሜርሃ ወማጎ ግሃ ወማድዮሃ፡ ወሞስክሃ ወቴር ሳሃ፤

ኢያፌትም ጎሜርን፤ ማጎግን፡ ማድዮንን፣ ሞስካንን፣ ቴር ሳስን ወለደ፤ እኒህ የያፌት ልጆች ናቸው፤

ወእሉ ውሉደ ኖኅ ፤

እኒህ ሁሉ የኖኅ የልጅ ልጆች ናቸው፤

፲፮፤ ወበሳፀወሰማኒት አዮቤላ ውስት አኀዘ ኖኅ የአዝዘ ለውሉደ ውሉዱ ሥርዐተ፤

በዛያ ስምንተኛው አዮቤልው ኖኅ ለልጅ ልጆቹ ሥርዓት ማዘዝን ጀመረ፤

ወትእዛዛተ ኵሎ ዘየአምር ወፍ ትሐ፤

የሚያውቀውን ትእዛዙን ፍር ዱን ያዝዝ ጀመረ፤

ወአስምዐ ላዕለ ውሉዱ ከመ ይግ በሩ ጽድቀ፤

በጎ ሥራን ይሠሩ ዘንድ በል ጆቹ ላይ አዳኘ፤

ወከመ ይክድኑ ኀፍረተ ሥጋ ሆሙ፤

በሰውነታቸው ያለ እርቃናች ውን ይሠውሩ ዘንድ፤

ወከመ ይባርክዎ ለዘፈጠሮሙ፤

የፈጠራቸው እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ዘንድ፤

ወያክብሩ አበ ወእመ፤

እናት አባታቸውን ያክብሩ ዘንድ፤

ወያፍቅሩ ፩ደ፡፩ደ ቢጸሙ፤

አንዱም አንዱ ባልንጀራውን ይወድ ዘንድ፤

ወይዕቀቡ ነፍሶሙ እምኵሉ ዝሙት፤

ሰውነታቸውን ከጋለሞታ ይጠ
ብቁ ዘንድ።

ወርኩስ።

ከኀልማሳ ሚስት፣ አንድም
ከብዙም ከጥቂትም ኃጢአት
ሰውነታቸን ይጠብቁ ዘንድ።

ወእምኵሉ ዓመፃ።

ከበደል ሁሉ ይጠብቁ ዘንድ
ያዝዛቸው ጀመረ።

እስመ በእንተ ዝንቱ ሠለስቱ ኮነ
አይኅ ላዕለ ምድር።

በእኒህ በሦስቱ ኃጢአት ምክ
ንያት ማየ አይኅ በምድር
ላይ ወርዶአልና።

፲፮። እስመ በእንተ ዝሙት ዘዘ
መዉ ትጉሃን እምትእዛዘ ኵነኔ
ሆሙ በድኅረ አዋልደ ሰብእ።

ትጉሃን ይባሉ የነበሩ ደቂቀ
ሴት የቃኤልን ልጆች በመከ
ተል ካዘዛቸው ሥርዓት ወጥ
ተው የማይገባ ሥራ ስለ
ሠሩ ማየ አይኅ መጥቶባቸዋ
ልና።

፲፯። ወነሥኡ ሎሙ አንስትያ
እምኵሎን እለ ኀረዩ ወገብሩ
መቅድመ ርኩሰ ።

መርጠው ከወሰዷቸው ሴቶች
ሁሉ ስቀድመው ኃጢአትን
ሠሩ።

ወወለዱ ውሉደ ናፊዲመ።

ኃያላን የሆኑ ልጆችን ወለዱ።

ወኵሎሙ ኢይትማሰሉ።

ሁሉም በመልክ አይመሳሰ
ሉም ቁመታቸውም ሦስት
ሺሕ፣ አንድ ሺሕ፣ ሁለት ሺሕ
ነው።

፲፱። ወይበልዕ ፩፩ዱ ካልኦ።

አንዱም አንዱ ባልንጀራውን
ይበላል።

ወቀተሎ ያርብሀ ለናፌል።

ናፌል ድኩም ማለት ነው፣
ያርብሀ ኃይለኛው ድኩሙን
ናፌልን ገደለው፤ ሦስቱ ሺሕ
ሁለቱን ሺሕ ይበላል።

ወናፌል ቀተሎ ለኤልዮ።

ናፌልም ኤልዮንን ገደለው።
ሁለቱ ሽሕ ሺሑን ይበላል።

ወኤልዮ ለዕንለ እመሕያው፣

ኤልዮም የሰውን ልጅ ገደለ፤
ሽሁ እንደኛ ያለውን ይበላል።

አንድም ኃይለኛው ደካማውን ይገድለዋል፤ ደካማውም የድኩም ድኩሙን ይገድለዋል፤ የድኩም ድኩም እንደኛ ያለ ነው፤

ወሰብእኒ ቢጸ፡

ባልጀራ ባልንጀራውን ይገድላል፤

ወዮሉ ተሰልጠ ይግበር ዓመፃ ፤

ሁሉም በደል ያደርግ ዘንድ ሰለጠነ፤ አንድም ተሠይጠነ ይላል፤ ባላጋራ ሆነ፤

ወከመ ይክዓው ንጹሐ ደመ ውስተ ምድር፤

ንጹሕ ደምን በምድር ላይ ያፈሰ ዘንድ ሰለጠነ፤

ወመልዐት ምድር ዓመፃ ምስለ ደም፤

ምድር ከደም ጋር በደሉን ሁሉ ሞላች፤

ወእምድኅረ እሉ፤

ከዚህ በኋላ ፤

ኵሎመ አራዊት ወአእዋፍ ፤

አራዊት አዕዋፍም ሁሉ፤

ወዘይትሐወስ ወዘያንሶሱ፤

ዲበ ምድር፤

በዚህ ዓለም የሚመላለሱ ወዲያ ወዲህ የሚሉ ሁሉ ጠፉ፤

፳፤ ወተክዕወ ደም ብዙኅ ዲበ ምድር፤

በምድር ላይ ብዙ ደም ፈሰሰ፤

ወኵሉ ሕሊና ወፈቃዱ ለሰብእ ይሄሊ ከንቶ፤

የሰው ፈቃዱ ሕሊናው ሁሉ ከንቱ ነገርን ያስብ ጀመር፤

ወእኩየ በዮሉ መዋዕል፤

ባለ ዘመኑ ሁሉ ክፉ ነገርን ያስባል፤

፳፩፤ ወደምሰሰ እግዚአብሔር ዮሉ እምገጸ ምድር በእንተ እስየ ምግባሮሙ፤

ስለ ክፉ ሥራቸው እግዚአብሔር ሁሉን ከዚህ ዓለም አጠፋ፤

ወበእንተ ደም ዘክዓዉ ዲበ ምድር ምስለ ዮሉ፤ ደምሰሰ ዮሉ፤

በዚህ ዓለም ስለ አፈሰሱት ደም ሁሉን አጠፋ፤

ወተረፍነ አነ ወአንትሙ ደቂ ቅየ፤

እኔና አናንተ ልጆቼ ቀረን፤ ወኵሉ ዘቦኡ ምስሌነ ውስተ ታቦት፤

ከኛ ጋራ ወደመርከብ ከገቡት ልጆቼ እኔና እናንተ ቀረን፤

፳፪፤ ወናሁ አነ እፌኢ ቀዳሜ ምግባሪክሙ ከመ ዘኢከንክሙ አንትሙ ዘተሐውሩ በጽድቅ፤

እናንተ በእውነተኛ ሕግ ጸን ታችሁ የምትኖሩ እንዳይደለ እኔ አስቀድሜ ሥራችሁን አየሁ፤

እስመ በፍኖተ ሙስና ወጠንክሙ ከመ ትሑሩ፤

በክፉ ሥራ ጸንታችሁ ትኖሩ ዘንድ ጀምራችኋልና፤

ወትትፋለጡ ፩፩ዱ እምነ ቢጹ፤

አንዱም አንዱ ከባልጀራችሁ ትለያያላችሁ፤

ወትትቃንኡ ዝንቱ ምስለ ዝንቱ፤

አንዱ በአንዱ ትቀናናላችሁ፤

፳፫፤ ወከመ ኢተሀልዉ ኅቡረ አውሉድየ ፩ዱ ምስለ እኁሁ፤

ልጆቼ አንዱ ከአንዱ ጋራ በአንድነት እንዳትኖሩ ትቀና ናላችሁ፤

እስመ እፌኢ አነ፤

እኔ አያለሁና ትለያያላችሁ፤

ወናሁ አጋንንት አስሕቶ ወጠኑ ላዕሌክሙ ወላዕለ ውሉድክሙ፤

እነሆ አጋንንት በናንተና በል ጆቻችሁ ላይ ማሳትን ጀመሩ፤

፳፬፤ ወይእዜኒ እፈርህ አነ በእን ቲክሙ ከመ እምድኅረ ሞትኩ አነ ትክዕዉ ደመ ሰብእ ዲበ ምድር፤

አሁንም እኔ ከሞትኩ በኋላ የሰውን ደም በዚህ ዓለም ታፈስሉላችሁ ብየ እኔ ስለና ንተ እፈራለሁ፤

ወትደመሰሱ አንትሙኒ እምገጸ ምድር፤

እናንተም ከዚህ ዓለም ትጠፋ ላችሁ ብየ እፈራለሁ::

እስመ ኵሉ ዘይክዑ ደመ ሰብእ፤

የሰውን ደም የሚያፈስ ሁሉ፤

ወኵሉ ዘይበልእ ደመ ዘሥጋ ይደመሰሱ ኵሎሙ እምድር፤

በሥጋ ያለውን ደም ሁሉ የሚበሉ ሰዎች ሁሉ ከዚህ ዓለም ይጠፋሉና ፤

ወኢይተርፍ ኵሉ ሰብእ ዘይበልዕ ደመ፤

ደምን የሚበላ ሰው ሁሉ፤

ወዘይክዑ ደመ ዲበ ምድር፤

በዚህ ዓለም ደምን የሚያፈስ ሰው ሁሉ ከሞት አይቀርምና ::

፳፩፤ ወኢይተርፍ ሎቱ ዘርእ፤

ልጅ፤

ወደኃሪት፤

የልጅ ልጅ፤

በታሕተ ሰማይ ሕያው፤

ከሰማይ በታች በዚህ ዓለም የሚኖር የለምና፤

እስመ ውስተ ሲኦል የሐውሩ፤

ወደመቃብር ይወርዳሉና፤

ወውስተ መካነ ደይን ይወርዱ፤

ጽኑ መከራ ወደአለበት ወደ ገሃነም ይወርዳሉና፤

ወውስተ ማዕምቀ ጽልመት ይትአተቱ ኵሉ፡ሙ በሞት ጸዋግ፤

በከፋ ሞተ ነፍስም ተይዘው ጽኑ ጨለማ ወደአለበት ይሄ

ዳሉና ዲያብሎስ ሕሱም ገጹን ጽሉም ራእዩን ያሳያቸዋል ደም ይደርቃል፤ ነፍስ ከሥጋ ትለያለችና ፀዋግ አለ፤

፳፪፤ ኵሉ ደም ኢያስተርኢ እም ኵሉ ደም ላዕሌክሙ፤

ደሙ ሁሉ ከደሙ ሁሉ ላይ ተለይቶ በናንተ ላይ አይገኝ፤

ዘውእቱ በኵሉ መዋዕል ዘጠባሕ ክሙ ኵሉ፤

ባለ ዘመናችሁ ሁሉ ያረዳች ሁት ደም ያሳጣችኋል፤

አርዌ ወእንስሳ ወዘይሰርር ዲበ ምድር፤

በዚህ ዓለም የሚበር የእንስሳ የአውሬ ደም ያሳጣችኋል፤

፳፫፤ ወግበሩ ምጽዋተ ላዕለ ነፍስክሙ በደፈኖቱ ዘይትከዓው ዲበ ገጸ ምድር፤

ርኅራኄ ነው፤ ለሰውነታችሁ ምጽዋት ይሆን ዘንድ ደሙን ቅበሩት፤

ወኢትኩኑ ዘይበልዕ ምስለ ደም፤

ብርንዶም ከሚበላ ሰው ጋር አንድ አትሁኑ፤

ወአጽንኡ ልበክሙ ከመ ኢትብ ልዑ ደመ ምስለ ሥጋ፤

ሥጋን ከደም ጋራ እንዳትበሉ በፊታችሁ ሕጋችሁን አጽኑ፤

በቅድሜክሙ ድፍኑ፤

በፊታቸሁ የአገኛችሁትን ደም ቅበሩት፤

፳፫፤ እስመ ከመዝ ተአዘዝኩ አስምዕ ለክሙ ወለውሉድክሙ ዘይመጽኡ ምስለ ኵሉ ዘሥጋ፤

ከሥጋዊ ከደማዊ ጋራ በልጆቻችሁም በእናንተም እንዲህ አዳኝ ዘንድ ታዝዣለሁና፤

ወኢትብልዕዋ ለነፍስ ምስለ ሥጋ፤

ነፍስን ከሥጋ ጋራ አትብላት፤

ከመ ኢይኩኑ ዘይትጋሠሡ ደመ ከሙ ዘነፍስክሙ እምእደ ኵሉ ዘሥጋ ዘይክዑ ደመ ዲበ ምድር፤

በዚህ ዓለም ደም ከሚያፈስ ከሥጋዊ ከደማዊ ሁሉ እጅ ነፍሳችሁ የምትሆን ደምን የሚመረምሯችሁ እንዳይ ሆኑ፤

እስመ ምድር ኢትነጽሕ እምነ ደም ዘተክዕወ ላዕሌሃ፤

ምድር በሷ ላይ ከፈሰሰው ደም አትነጻምና ነፍስን ከሥጋ ጋር አትብሏትና፤

እስመ በደመ ዘከዓም ትነጽሕ ምድር ፡ እምርኵሳ በኵሉ ትዝ ምዱ፤

በዘመኑ ሁሉ ምድር ደምን በአፈሰሰ ሰው ደም ትነጻለችና፤

፳፬፤ ወይእዜኒ ውሉድየ ስሙ ዑኒ፤

ልጆቼ አሁንም ስሙኝ፤

ወግበሩ ፍትሐ ወጽድቀ ወርትዓ ከመ ትተከሉ በጽድቅ ውስተ ገጸ ኵሉ ምድር፤

በዚህ ዓለም በእውነት ሥራ ጸንታችሁ ትኖሩ ዘንድ፤ እውንት ነገርን ተናገሩ የቀና ፍርድን ፍረዱ፤

ወይትሌዓል ክብርክሙ በቅድመ አምላኪየ ዘአድኃነኒ እምነ ማየ አይኅ ፡

ከማየ አይኅ፤

ባዳነኝ በፈጣሪየ ፊት ክብራችሁ ይበዛል፤

፳፭፤ ወናሁ አንትሙ ተሐውሩ ወተሐንጹ ለክሙ አህጉረ፤

እንሆ እናንተም ሂዳችሁ ሀገር ታቀናላችሁ፤

ወትተክሉ ውስቴቶን ኵሉ ተክለ ዘዲበ ምድር፤

በውስጣቸውም በዚህ በምድር ላይ ያለውን ተክል ሁሉ ትተ ክላላችሁ፤

ወኵሉኬ ዕፅ ዘይፈሪ ፫ዓመተ ይከውን ፍሬሁ ዘኢይትቀሠም ለበ ሊዖቱ፤

የአፈራውን እንጨት ሁሉ በሶስተኛው ዓመት የሚደርሰ ውን ለመብላት ፍሬውን መል ቀም አይገባም::

፴፩፤ ወበራብዕ ዓመት ይትቄደስ ፍሬሁ፤

ባራተኛው ዓመት ፍሬው ለቤተ እግዚአብሔር ይለይ፤

ወየዐርጉ ቀዳሚ ፍሬሁ ዘይሰ ጠው ቅድመ እግዚአብሔር ልዑል ዘፈጠረ ሰማየ ወምድረ፤

ሰማይንና ምድርን በፈጠረ በእግዚአብሔር ፊት ወዶ ሊቀ በለው መጀመሪያ የደረሰውን ፍሬውን ያቀርባሉ፤

ወኵሉ ያዕርጉ በጥሉል ቀዳሚ ወይን፤

መጀመሪያ የደረሰውን ወይን፤

ወቅብዕ፤

ዘይቱን፤

ወቀዳሚ ፍሬ፤

መጀመሪያ የደረሰውን ፍሬ፤

ውስተ ምሥዋዐ እግዚአብሔር ዘይ ትዌከፍ፤

መሥዋዕቱን ወደሚቀበል ወደ እግዚአብሔር ያቀርቡታል፤

ወዘተርፈ ይብልዑ ላእካነ ቤተ እግዚአብሔር በቅድመ በምሥዋዕ ዘይትዌከፍ፤

ከመሥዋዕቱ የቀረውን እግ ዚአብሔርን የሚያገለግሉ ካህ ናት በምሠዊያው ፊት ይብሉ::

፴፪፤ ወበዓመት ሐምስ ግቡሩ ጎድጎተ፤

ባምስተኛው ዘመን የደረሰውን ለራሳችሁ አድርጉ፤

ከመ ትጎድግዎ አንትሙ በጽድቅ ወበርትዕ፤

እናንተ በእውነቱ ነገር በቀና ነገር ተክላችሁን ሁሉ ትተዉ ዘንድ

ወትጸድቁ፤

ትከብራላችሁ፤

ወይረትዕ ኵሉ ተክልክሙ፤

ተክላችሁ ሁሉ የቀና ይሆ ናል፤

እስመ ከመዝ አዘዞ ሄኖክ አቡሁ ለአቡክሙ ማቱሳላ ወልዱ።

የአባታችሁ አባት ሄኖክ ልጁን ማቱሳላን እንዲህ አዞታልና።

ወማቱሳላ ለላሜህ ወልዱ።

ማቱሳላም ልጁ ላሜህን እን ዲህ አዞታልና።

ወላሜህ አዘዘኒ ኵሎ ዘአዘዝዎ አበ ዊሁ።

ላሜህም እኔን ልጁን አባቶቹ ያዘዙትን ሁሉ አዝዞኛልና።

፴፫። ወአነሂ እኤዝዘክሙ ውሉ ድየ በከመ አዘዞ ሄኖክ ለወልዱ።

ሄኖክ ልጁን እንዳዘዘው እኔም አዛችሁአለሁ።

በቀዳሚ ኢዮቤላውስት እንዘ ሕያው ውእቱ ውስተ ትዝምድ ላብእ።

በመጀመሪያው ኢዮቤልዩ በሰ ባተኛው ትውልድ በሕይወተ ሥጋ ሳሉ አዘዘ።

ወአስምዐ ለወልዱ ወለውሉደ ውሉዱ እስከ አመ ዕለተ ሞቱ ለማ ቱሳላ።

ማቱሳላ እስከ ሞተበት ቀን ድረስ ለልጁ፣ ለልጆቹ ልጆች አዘዘ አዳኘ።

፴፬። ወበሳወይ ኢዮቤልዩ በሱ ባዔ ቀዳማዊ ዘቀዳሚሁ ነሥአ ሎቱ አርፋስክድ ብእሲተ።

በሃያ ዘጠነኛው ኢዮቤልዩ በመጀመሪያው ሱባዔ በሦስተ ኛው ዓመት አርፋስክድ ሚስ ትን አገባ።

ወስማ ራሱዕያ።

ስሚም ራሱእያ ትባላለች።

ወለተ ሱሳን፣ ወለተ ኤላም ሎቱ ብእሲተ።

ይችውም የኤላም ልጅ የምት ሆን የሱሳን ልጅ ሚስት ትሆ ነው ዘንድ ወሰደ።

ወወለደት ሎቱ ወልደ።

ወንድ ልጅን ወለደችለት።

በዓመት ሣልስ ዘሱባዔ ዝንቱ።

በዚህ ሱባዔ በሶስተኛው ዓመት ወለደችለት።

ወጸውዐ ስሞ ቃይንም።

ስሙንም ቃይንም ብሎ ጠራው። አርፋስክድ ቃይን ምን፣ በመቶ ዐሥራ ዘጠኝ ዘመን ወልዶታል። ይህን

ቢያገናኙት ሽሕ ክሶስት መቶ ሰባ አምስት ዘመን ይሆናል፤ ሽሑ ሃያ ኢዮቤልዩ ሃያ ዘመን ይሆናል፤ ሦስት መቶ ስድስት ኢዮቤልዩ ስድስት ዘመን ይሆናል፤ ስድስቱን ከሃያው ሲገጥሙት ሃያ ስድስት ይሆናል ፤ ሃያ ስድስቱን ከሰባ አምስቱ ሲገጥሙት መቶ አንድ ይሆናል፤ ከመቶው ሁለት ዘመን ሲያ ነሱለት ሁለት ኢዮቤልዩ ይሆናል፤ ከሃያ ስድስት ኢዮቤልዩ ሲገጥሙት ሃያ ስምንት ኢዮቤልዩ ሁኖ ሶስት ዘመን ይተርፋል፤ ስለ ተጀመረ ሃያ ዘጠኝ ኢዮቤልዩ አለ።

ወልህቀ ወልዱ፤

ልጁ ቃይንም አደገ፤

ወመሀሮ አቡሁ መጽሐፈ፤

አባቱ መጽሐፈ አበውን አስተማረው።

ወይእ፤ ወሖረ ይኅሥሥ ሎቱ መካነ ኀበ ይኅዝ ሎቱ ሀገረ፤

ሀገር የሚያቀናበትን ቦታ ይፈልግ ዘንድ ሄደ፤

ወረከበ መጽሐፈ ዘቀረጹ፤ ቀደምት አበው ውስተ ኮኮሕ፤

የቀደሙ ሰዎች በድንጋይ የቀረጹትን መጽሐፍ አገኘ፤

ወአንበበ ዘውስቴታ፤

በውስጧ ያለውን አነበበ፤ ወአዕለዋ፤

ቀዳት መለሳት፤

ወረሰአ እምውስቴታ ከመ ሀሎ ውስቴታ ትምህርት ዘትጉሃን፤

የመላእክት ትምህርት በውስጧ እንዳለባት ዘነጋ፤

በዘይፌእዩ ሠረገላ ፀሐይ ወወርኀ ወከዋክብት ወውስተ ኵሉ ተአምረ ሰማይ፤

በሰማይ የሚደረገውን ምልክት ሁሉ የጨረታ የከዋክብት የፀሐይ ሠረገላ እንዳለ ዘነጋ።

ወይእ፤ ወጸሐፋ፤

ጻፉት፤

ወኢነገረ በእንቲአሃ፤

የእርሷን ነገር አልተናገረም፤

እስመ ይፈርሆ ለኖኅ ነጊረ በእንቲአሃ፤

የርሷን ነገር ለኖኅ መናገር ይፈራልና፤

ከመ ኢይትመዐዕ ላዕሌሁ በእንቲ አሃ።

በእሷ ምክንያት እንዳይቆጣው ይፈራልና።

፴፯። ወበ፴ ኢዮቤልው በሱባዔ ካልዕ በቀዳሚ ዓመት ነሥአ ሎቱ ብእሲተ።

በ፴፩ው ኢዮቤልዩ በሁለተኛው ሱባዔ በመጀመሪያው ዓመት ሚስትን አገባ።

ወስማ ሚልካ።

ስሟም ሚልካ ይባላል።

ወለተ አፀዳይ ወልደ ያፌት።

የያፌት ልጅ የሚሆን የአፀዳይ ልጅ ናት።

፴፪። ወበዓመት ራብዕ ሎቱ ወለደ ወልደ።

ባራተኛው ዘመን ወንድ ልጅን ወለደ።

ቃይናን ሳላን በሃምሳ ሰባት ዘመን ወልዶታል። ቢያገኙት ሽሕ ከአራት መቶ ሠላሳ ሁለት ይሆናል ይህ ሃያ ዘጠኝ ኢዮቤልዩ ሁኖ ዐሥራ አንድ ዘመን ይተርፋል። ስለ ተጀመረ እንዲህ አለ።

ወጸውአ ስሞ ሳላ።

ስሙን ሳላ ብሎ ጠራው።

ተፈንዎ ማለት ነው።

እስመ ተፈንዎ ተፈናኩ።

መላክን ተልኬአለሁና።

ወልህቀ ሳላ ።

ሳላም አደገ ።

ወነሥአ ሎቱ ብእሲተ ።

ሚስትን አገባ።

ወስማ ሞዓክ ወለተ ኬሴድ እኅወ አቡሁ ሎቱ ብእሲተ።

ሚስት ልትሆነው ስሟ ሞአክ የተባለችውን ሴት አገባ። ይችውም ያባቱ ወንድም የኬሴድ ልጅ ናት።

፴፫። ወበዓመት አሐዱ በ፴ ወ፩ ኢዮቤልዩ።

በአንድ ዓመት በሠላሳ አንድ ኢዮቤልዩ።

በሱባዔ ሐምስ በቀዳሚ ዓመት ወለደት ሎቱ ወልደ።

ባምስተኛው ሱባዔ በመጀመሪያው ዓመት ወንድ ልጅ ወለደችለት።

በሐምስ ዓመቱ ሎቱ ጸውዐ ስሞ ኤቦር።

በአምስተኛው ዓመት ስሙን ኤቦር ብሎ ጠራው፤ ሳላ ኤቦ ርን በሰባ አንድ ዘመን ወልዶ ታል ቢያገናኙት ሽሕ ከአም ስት መቶ ሶስት ይሆናል፤ ይህ ፴ ኢዮቤልዩ ሁኖ ሠላሳ ሶስት ዘመን ይተርፋል፤

ይህን በሱባዔ ቢገቡት ዐራት ሱባዔ ሆኖ አምስት ዓመት ይተርፋል አለ፤ ስለተጀመረ እንዲህ አለ፤

ወነሥአ ሎቱ ብእሲተ፣

ሚስት አጋባው፤

ወስማ አዙራድ ወለተ አብሮድ፤ የአብሮድ ልጅ ስሟም አዙራድ የምትባል፤

፵፤ወበ፴ ወ፪ ኢዮቤልዩ በሱባዔ ሳብዕ በሣልስ ዓመቱ፤

በሠላሳ ሁለተኛው ኢዮቤልዩ በሰባተኛው ሱባዔ በሦስተኛው ዘመን፣

ወበሳድስ ዓመት ወለደት ሎቱ ወልደ፤

በስድስተኛው ዓመት ወንድ ልጅን ወለደችለት፤ ኤቦር ፋሌክን በሠላሳ አራት ዘመን ወልዶታል ቢያገናኙት ሽሕ ካምስት መቶ ሰላሳ ሰባት ሱባዔ ሊሆን አንድ ዘመን

ይቀረዋል የቀረው ጥቂት ስለ ሆነ እንዲህ አለ፤

ወጸውአ ስሞ ፋሌክ፤

ስሙን ፋሌክ አለው ክፍለት ማለት ነው፤

እስመ በመዋዕሊሁ ዘተወልዱ ደቂቀ ኖኅ አኀዙ ይትካፈሉ ሎሙ ምድረ፤

በዘመኑ የተወለዱ የኖኅ ልጆች ምድሩን ሊካፈሉ ጀም ረዋልና።

ወበእንተዝ ጸውዐ ስሞ ፋሌክ፤

ስለዚህ ነገር ስሙን ፋሌክ ብሎ ጠራው፤

ወተካፈሉ በእኩይ በበይናቲሆሙ፤

እርስበርሳቸው በጠብ ተካ ፈሉ፤

ወነገርዎ ለኖኅ፣

ለኖኅም ነገሩት።